ማውጫ

ተ.ቁ	አርዕስት	ገጽ
1/.	ማውጫ	1-4
2/.	መግቢያ	5-10
3/.	የናት ኢትዮጵያ ምክር	10-11
4/.	ጀግኖች ሕያው ናችሁ	11-14
5/.	ማነው እሱ	15-16
6/.	ለሠላም ለፍቅር	17-18
7/.	ቀን ማታ ገዳይ	18-20
8/.	የኋላ የኋላ	20-21
9/.	ለጉዞኛው	21-23
10/.	ምነው ድሮ በኖርኩ	23-24
11/.	ትዝ እለኝ አገሬ	24-25
12/.	ከእገሩ የወጣ እገሩ እስኪመለስ	25-27
13/.	እንክርዳድ ከስንዴ	27-28
14/.	መቼ ተማርን	28-28
15/.	ውቧ እናት	29-30
16/.	ፖለቲካ መብት ነው	30-30
17/.	የፈለሰ ውኃ	30-3ነ
18/.	መሬት ላራሹ	31-32
19/.	የኛ ድርሻ	32-33
20/.	የእበሻ ልጅ	33-33
21/.	ኢትዮጵያ የኛ ናት	33-34
22/.	መድሀኒት እንቀምም	34-34
23/.	አያድርስ	34-35

ልጅ ከወላጁ ምን ይቀስማል።

አባት ከአካሉ ከፍሎ በአምሳሉ ያመጣውን ልጁን ከሕፃንነት እስከ ዕውቀት፤ ይገራል፤ መንገድ ያሳያል፤ ገና ከእንቦቃቅላነቱ ጀምሮ እየደገፈ ከቤት ውጪ በማውጣት አካባቢውና ተፈጥሮ ስለው ልጆች ያደላቸውን ሁሉ እንዲያውቅ ያደርጋል። ራሱን ማወቅ ሲጀምር በተረትና በታሪክ እያስመሰለ እንደ አስፈላጊነቱም ጠቁሞ እያሳየ የቀሰምና የኑሮ ዘዴን፤ የቤተሰቡን የሕዝቡን ታሪካዊ መሠረት፤ ደንብ፤ እምነት፤ ምንነቱና ማንነቱን ያመለክተዋል። ራሱን መቻል ሲጀምር፤ የአስባበስ፤ የአመጋገብ ሥርአትን፤ ከሰዎች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት የአቀራረብ ስልትን፤ የሥራ ክቡርነትን፤ የመኖሪያው፤ የአካባቢውና፤ የአገሩን ዳር ድንበር፤ ራሱን፤ ቤተሰቡንና አገሩን ከጥቃት የመከላለል ዘዴ፤ ወ.ዘ.ተ ያስጨብጣል። አባት አስገድዶ ያሠራል አዞ ያስፈጽማል። ይመከራል፤ ይገሰፃል፤ ይቀጣል።

እናት የልጇና የቧ አካል አንድ ላይ ተጣብቀው ከተዛመዱበት የሚለያዩት በልደት ጊዜ በስስት ሲሆን ሁለተኛው በሞት ነው። እናት ርህሩ ነች። ከራስዋ አብልጣ ልጇን ስለምትወድ እንቅልፍ አጥታ ሁሉንም ነገር ስለጅ ነው፤ በዚህ ላይ ምንም ጉዳት በልጆችዋ እንዳይደርስ ስለምትፈልግ ከአይኗ እንዳይርቁ ትሻለች። እናት ከምትፈልገው ይበልጥ የምትሰጥ ከምታሠራው ይበልጥ የምትሠራ የፍቅር ምንጭ የፍቅር ተምሳሊት ናት።

ቤተሰብ የመጀመሪያው ትልቁ ት/ቤት ስለሆነና አባቶቻችን ከዚያ በተማሩት አብዝተውና ከቀለም ትምሕርት ጋር አቀናጅተው በመጠቀማቸው ራሳቸውና አገራችን ኢትዮጵያ ተከብረው ጀግና ሕዝብ ሃያል አገር ተብለው ስብዙ ሺ ዓመታት እንዲቆዩ አድርገዋል.....»

ተ.ቁ	አ ር ዕ ሰ ት	ገጽ
24/.	ደርጎች	35-37
25/.	ሳቁን ገደሉብኝ	37-39
26/.	የአብዮቱ ዘመን አሽሙሮች	39-39
27/.	አድዋ ዛሬ ቢሆን	40-40
28/.	ነጋዴዎች	40-40
29/.	እናቴን ሰረልግ	40-41
30/.	አገሬ ቆንጆ ናት	41-41
31/.	ትዳር እሹሩሩ	41-42
32/.	ስደተኞች ድሆች	43-43
33/.	የዚህ ዓለም ኑሮ	43-44
34/.	አመዛዝኖ መርገጥ	44-44
35/.	ሰልጣኔና ሰው	44-44
36/.	የሰው ልጅ ይረሳል	45-45
37/.	ምን ይዞ ጉዞ	45-46
38/.	ሥኳር የበዛበት	46-46
39/.	በማሰረጃ ይሁን	46-46
40/.	የነቃ ሕዝብ	47-47
41/.	አባይ ባንደበቱ	47-49
42/.	አሜሪካን አገር	49-51
43/.	ብትር	51-52
44/.	ቀጠሮ ይከበር	52-53
45/.	የክሬዲት ምስጢር	53-55
46/.	የእንድ ሰሞን ሕብረት	55-55
47/.	ጣሊያንና እንግሊዝ	55-56

ተ.ቁ	አ ር ዕ ሰ ት	ገጽ
48/.	ሥርአት ሲያረጅ	56-57
49/.	ከአቅም በላይ መኖር	57-59
50/.	አለን አንዳንድ ሰዎች	59-60
51/.	ገመድ ጉተታ ላይ ነን	60-60
52/.	ለከሃዲና ጨካኙ ጓደኛዬ	60-61
53/.	የኢትዮጵያ ምድር	61-62
54/.	ማነው ኢትዮጵያዊው	62-63
55/.	ዓለም	63-64
56/.	የተስፋ ምድራችን	64-67
57/.	ትጉህ ገበሬ	67-68
58/.	መሪዮቻችንን ሰንመርጥ	68-68
59/.	ሞት ራሱ እንዲሞት	68-69
60/.	ስልክ በደበሪያ ሆነ	69-70
61/.	ታሪክ አይረሳውም	70-71
62/.	ራሳችን እንምከር	71-72
63/.	ለከቡር አቶ ሰይፈ ታደሰ	72-73
64/.	አባይን እንክሰስ	73-74
65/.	አዋሽ	74-74
66/.	ምንድነው ራዕያችን	75-76
67/.	ፖለቲካና ዘር	76-76
68/.	አሳማና ዝሆን	76-77
69/.	ምስጢሩ ምን ነበር	77-77
70/.	የጎረቤት ያለህ	78-78
71/.	ምን ውለአቸው ይሆን	78-78

ተ.ቁ	አ ር ዕ ስ ት	ገ ጽ
72/.	ጠላትን እናላፍር	78-79
73/.	የእገርህ ድርሻ	79-80
74/.	የጥንቱ ኢትዮጵያዊነት	80-80
75/.	እስቲ ልብ እንግዛ	80-81
76/.	ወርቅ በሳት ይፈተናል	81-82
77/.	ድሮና ዘንድሮ	82-83
78/.	የእግር ኳስ	83-83
79/.	ሀያሉ ፍቅር	84-85
80/.	ሕዝብ ይጠብቃል	85-85
81/.	መንግሥትም እንደሰው	85-88
82/.	ሉሲ በአሜሪካ	88-88
83/.	ትዳር በጥቃቅን ችግር	88-88
84/.	ሰውጭ በዝባዦች	88-90
85/.	ይድረስ ለወ/ ዓለም ፀሐይ ወዳጆ	90-91
86/.	ይድረስ ለሎሬት ፀጋዬ ገ/መድሕን	91-95
87/.	ይድረስ ለፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም	95-87
88/.	ይድረስ ለሎሬርት ሜትር አፈወርቅ	97-88
89/.	መዝሙር	98-98
90/.	አበርክቶትና ምስጋና	99-100

መግቢያ

ልማትና ጥፋት በሁለት ተቃራኒ ጎራ የሚገኙ ክስተቶች ሲሆኑ የአንድ አገር እጣ ፋንታ በሰዎች ቀጥታና ተዘዋዋሪ ከንዋኔ እማካኝነት ከሁለቱ አቅጣጫዎች ወደ እንዱ ሊያመራ ስለሚችል ዜጎች በዚህ ዓለም በሚኖሩበት እጭር ጊዜ ውስጥ ንቁ ተሳትፎና እርምጃ እጅግ ወሳኝነት አንዳለው የታወቀ ስለሆነ ስሚሆነው ነገር ሁሉ ሀላፊነትና ግዴታ እለባቸው።

አገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ እንደ ተገለጸው እጅግ ታላቅና ገናና እገር እንደነበረችና ግዛትዋም ከግብጽ እስከ ኬንያ፤ ከሱዳን እስከ ሕንድ ውቅያኖስ ጠርፍ እንደነበረ፤ በአክሱም ዘመነ መንግሥት በ3ኛው ክፍለ ዘመን ደግሞ በሥልጣኔና በኃይል ሚዛን በዓለም ኃያላን ከሚባሉት አራት መንግሥታት ማለትም ከፋርስ፤ ከሮማና ከቻይና አንዱ ሆና ለብዙ ዘመናት እንድቆየችና ለሌሎች አግሮች ነፃነት ጭምር በመቆም፤ ቀይባሕርን ራስዋ በሠራቻቸው ዘመናዊ መርከቦች እቋርጣና ወታደር አዝምታ እስከ እስራኤል፤ አረቢያና የመን ድረስ በመሄድ መካከለኛው ምስራቅን ሁሉ ትቆጣጠር እንደነበረ፤ በላሊበላና በጎንደር ስርወ መንግስታት ጊዜም ከሞላ ጎደል ሉዓላዊነቷ፤ ክብሯና፤ የሕዝቧ የተረጋጋ ሕይወት ተጠብቆ ለዘመናት እንደቆየች ከታሪክ እንረዳለን።

ኢትዮጵያ በታሪኳ ታይቶና ተሰምቶ የማይታወቅ የውድቀት ቁልቁለት ጉዞ የጀመረችው በመነ መሣፍንት

በመባል ከሚታወቀው ወቅት ጀምሮ ነው ሰማሰት የሚቻል ሲሆን በዚያ ዘመንም ቢሆን ሉዓላዊነቷ ተጠብቆ ቆይቷል። ነገር ግን ብዙ መሳፍንት በየበታው ተነስተው እርስ በእርሳቸው በሚያካሂዱት ፉክክርና በሚፈጥሯቸው ግጭቶች ምክንያት አገራችን ማዕከላዊነት በጎደለው አስተዳደር ተከፋፍላ በመቆየቷ ሰብዙ ሺዮች ዓመታት ያካበተቻቸውን ፤ሐብት፤ ሥልጣኔ፤ ታሪክ፤ የብሔርና የብሔረሰቦች የፍቅር አኗኗርና ሌሎችም አሴቶች ሁሉ መዳከም የጀመሩበት ጊዜ ነበር።

በብዙ ወንዞች ተከባ በማዕድናት፤ በልምላሜና በአስትራቴጂያዊ አቀማመጥዋ በመበልጸጓ የነመጁትና የራሳቸውን ሰማድረግ ፅንቅልፍ ያጡትም የአገሪቷ ታሪካዊ ጠላቶች ይሆንን አመቺ ሁኔታ ሲያገኙ ፊታቸውን እዙረው የወረራ ስልት ያቀናጁበት ዘመንም እንደነበረ እንረዳለን። ከዚያ ከዘመነ መሳፍንት ጀምሮ ይሽውና እስከዛሬ ድረስ አገራችን ኢትዮጵያና ልጆቿ በተለያየ መልክ በሚቀነባበሩ የጠላት ተንኮል አዙሪት ውስጥ ገብተው እየዳከሩና መስዋዕትነትም እየከፈሉ ይገኛሉ።

በአፄ ቴዎድሮስ፤ በአፄ ዮሐንስ፤ በአፄ ምኒልክ፤ በንግሥተ ነገሥታት ዘውዲቱ፤ በአፄ ኃይለሥላሴ፤ በደርግና በኢሃዴግ ዘመን መስተዳድሮች ከውጭ ወራሪዮችና በአገር ውስጥ በተፈጠሩ የእርስ በእርስ ግጭቶችና ያለመረጋጋት የተነሳ የወደመው የአገር ኃብትና የባከነ የሰው ኃይል እጅግ ብዙ በመሆኑ አገራችንና ሕዝባችን

በድሕነት አረንቋና በኋላ ቀርነት ውስጥ ገብተው እንዲያዘግሙ ተገደዋል ። በመሆኑም ዜጎች የዕለት ምግብና ወቅታዊ መፍትሔ ፍለጋ እጅግ ትናንሽና በጣም ድሃ ከሚባሉ አገሮች ውስጥ ሳይቀር ተበትነው በስደት ላይ የሚገኙ ሲሆን በጉዞ ላይ ጨካኞች፤ አረመኔዎች፤ የበረሓ ንዳድና የባሕር ማዕበል ፈጅቷቸው ካስቢቸው አገር የሚደርሱ ቢኖሩ ጥቂቶች ናቸው። ያም ሆኖ እንደ ሳውዲ አረቢያ፤ የመን፤ ሊባኖስ፤ ሲሪያ፤ ግብጽ፤ ወ.ዘ.ተ በመሳሰሉ አገሮች አሠሪዎቻቸው የለው ጀርባ ሲሸከመው በማይችል ዘግናኝ ጭቆና እየተፈጸመባቸው ሕይወታቸው የሚቀጠፍ እጅግ ብዙዎች ናቸው። ከዚህም ባሻገር በደቡብ አፍሪካ ውስጥ ዛይሎ ፎቢያ በተለኘ ጠባብ አስተሳሰብ በተለከፉ ዘረኞች እያሌ ኢትዮጵያውያን ጥረውና ግረው የቋጠሩትን ንብረት ተዘርፈዋል፤ ሕጻናት ሳይቀሩ በአሳት ተቃጥሰው የተገደሉ ሲሆን ከአገር የተባረሩና በየእስር ቤቱ የሚማቅቁ እንዲሁም በሊቢያና በመሳሰሉ አገሮች በአከራሪዎች የታረዱ ዜጎች ከብዙ በጥቂቶች በምሳሌነት መዋቀሱ ይበቃል። ለነዚህ ዓይነቶቹ የአገራችን ችግሮች መነሻ የሆኑ እያሌ ውጪያዊና የውስጥ ምክንያቶች መኖራቸው ቢታወቅም እኛ ኢትዮጵያዊያን ግን ከተጠያቂነት ነፃ ልንሆን አንችልም። ምክንያቱም ከላይ በመግቢያው ላይ እንደገለጽኩት እነዚህ ብዙዎቹ ሰው ሠራሽ ችግሮች እንዲኖሩ በቅየታና በተዘዋዋሪ ፈቅደናልና። የችግሩ ጥልቀትና የመፍትሔው ውስብስብነት ሲታይ አቡነ

ቀውሰመሰ የተባሉት አባት ይግባኝ ለክርስቶስ በተሰኘው መጻፋቸው እንዳስቀመጡት ስሚ የጠፉ ቢሆንም ነገር ግን ዜጎች የሆንን ሁሉ በመካከላችን ያሉትን አንቅፋቶች አስወግደንና በርትተን ከሠራን ሌሎች የበለጸጉ አገሮች የደረሱበትን ቦታ ለመድረስ የሚከለክለን ነገር ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ካለፉት ችግሮች ትምሕርት ቀስመን ባጭር ታትቀን በመነሳት ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል። የአንድ አገር ከፉና ደግ ውጤቶችን በጋራ ተጥቃሚ ሆነው የሚኖሩ ብሔር ብሔረሰቦች ተከባብረው አንደ አንድ አገር ዜጎች በፍቅር እንዲኖሩ፤ የአገሪቷ ሃብት ለአገሪቷ ዜጎች በተስተካከለ ሁኔታ እንዲዳረስ፤ ነጋዴውና ገበሬው ሠርቶ አገሩንና ራሱን እንዲረዳ የሰከነ የሥራ መንፈስ ተመቻችቶ ተግቶ አንዲሰራ፤ ምሁሩ በአገሩ ቆይቶ ልምዱንና ሙያውን ለአገር ጥቅም እንዲያውል፤ አዲሱ ትውልድ በትምህርት ገፍቶ በሰላማዊ መንገድ የሚቀጥለውን አገር ለመምራት የሚያስችል አውቀትና ልምድ አግኝቶ እንዲዘጋጅ፤ የሥራ አጥ ቁጥር እንዲቀንስ፤ የዕለት ምግብና መጠለያ አጥተው በሚሰቃዩ ድሃ ዜጎችና በጥቂት ቱጃሮች መካከል ያለው የሰግይና ምድር ያህል ልዩነት እንዲጠብ ሕዝብ በአገሩ ጉዳይ ሳይ በትጋትና በንቃት ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ወ.ዘ.ተ ብዙ ጥረት መደረግ ይገባል የሚል አምነት አለኝ።

ከዚህ በመነሳት ዜጎች ሀሳባቸው ከሚገልጹባቸው መንገዶች አንዱ ሥነጽሁፍ እንደመሆኑ መጠን እኔም

እንደማንኛውም አገር ወዳድ ዜጋ ከሳይ ለመግለጽ የሞከርኳቸውና ባለለፍኳቸው የዕድሜ ዘመናት ካጋጠሙኝ ውጣውረዶች የተነሳ የተረዳኋቸውን ችግሮችና በአንባራቸው መፍትሄ ይሆናል ያልኳቸውን ሀሳቦች በንጹህ ህሊናና ቅን ልቦና ተነሳስቼ በዚሁ ይድረስ ለኢትዮጵያውያን በተሰኘ ትንሽ መጽሀፍ ውስጥ በየአምዱና በየአርእስቱ ከፋፍዬ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ። ሠላማዊና ሕጋዊ በሆነ መንገድ ሃሳብን መግለጽ ዲሞክራሲያዊ መብት ከመሆኑም ባሻገር የሠለጠኑ አገሮችና መንግሥታት የሚያበረታቱት ሕገመንግስታዊ መብትም ነው። ዜጎች በተለያየ መንገድ ከሚሰጡት የሳብ በመማግር ተገቢ ምላሽ መስጠት ለአንድ አገር አድገት እጅግ ጠቃሚ ከመሆኑ ባሻገር ዛሬ በኤኮኖሚ የበለጸጉ አገሮች የሄዱበት መልካም ጎዳና በመሆኑ ሀላፊነት የተጣለብን ዜጎች ሁሉ ከዚህ ተገንዝበን የአገራችንና የሕዝባችን ችግሮች ከኛ እንዳያልፉ በመገደብ ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የምናስረክባቸውን መልካም ነገር ማዘጋጀት የሚገባን ጊዜ ነው የሚል ሀሳብ አለኝ።

ስለሆነም ለአገራችን ውድቀትም ሆነ ልማት ተጠያቂው እኛ የወቅቱ ትውልድ የሆንን ዜጎች መሆናችን ተገንዝበን ታሪክ የጣለብንን ሀላፊነት እንድንወጣ አሳስባለሁ።

የዚህን ትንሽ መጽሐፍ ረቂቅ የተመለከቱ ወዳጆቼ አነሱ፤ በዙ በማለት የጠቆሙኝን አስተካክያለሁ ምናልባትም የቀረ ነገር ካለ ለወደፊት አንባቢያን በሚያቀርቡት ጥቆማ

መሰረት ሰማሸሻል ዝግጁ ነኝ፤ከዚህ በተረፈ ማንንም
ሰመውቀስ ዓላማና ፍላጎት እንደሌሰኝ አንባቢያን ወገኖቼ
እንዲረዱልኝ በትህትና እጠይቃሰሁ።
የአገራችን ኢትዮጵያ ሉአላዊነት ተከብሮ ጦርነትና
ግጭቶች ተወግደው፤ ድህነት፤ስደት፤ረሓብ፤ድርቅና
በሽታ ጠፍቶ፤ከምሰራቅ እስከ ምእራብ ከሰሜን
እስከደቡብ ሰላም ፍቅር ሰፍኖ፤ሁሉም ዜጋ ድምጹ
ተሰምቶ፤መብቱ ተጠብቆሰት፤የሚፈልገውን በማግኘቱ
ተደስቶና አምሮበት ሰማየት እንድንችል እግዚአብሔር
በቸርነቱ ይርዳን። መልካም ዘመን ብሩህ ተስፋ ያድሰን
እሜን ! !

መልካም ንባብ

*የናት ኢትዮጵያ ምክር

ከተሜ ባላገር ነጋዴ አርሶ አደር
ተማሪ መዛደር ምሁራን ወታደር
ሳትከፋፈሉ በሐይማኖት በዘር።
ልጆቼ ወገኖቼ እየኝ ልታያችሁ
ያጎረስኩበትን ጣቶቼን እይታችሁ
ያጠባሁበትን ጡቴን አስታውሳችሁ
ብዙ ማስረጃ አለኝ የኔ ልጆች ናችሁ
እህት ወንድም ናችሁ አንድ ሁኑ እባካችሁ።
ከአንድ እናት ተወልዶ ሰየብቻ መቆም
መንገዱ ጉጂ ነው የትም አያደርስም
እናም አንድ ሆኑ እሱ ብቻ ይበቃል
ጠላት ስቆብናል በልግት በልጦናል

ቤተሰብ ጎረቤት አልፎን ጥሎን ሄዷል
መድረስ ያስፈልጋል መቅደም ያስፈልጋል
በሕብረት ጥላ ስር ጥረት ሁሉ ይሳካል
የሄደው ይመጣል የታጣው ይገኛል
የናት አገራችሁ የሕዝባችሁ ችግር ባጭሩ ይቀጫል።
ውስብስቡ ችግር ጥልፍልፉ ተንኮል ይፋ ይገለጻል።
ምክሬን ተቀበሉኝ ፍቅር መስርቱልኝ
በእናት እንድ ናችሁ ደግችሁ እንድ ነው እንድ ልብ
ሁኑልኝ
የእናትነት ክብር ወግ ማዕረግ ይድረሰኝ
ቃሌን ተቀበሉኝ ኑዛዜዬን ስሙኝ
በሰላም በፍቅር ሁሉም ነገር ያምራል
ሰቅሶ እንኳን ይደምቃል።
ልጅ አንድ ከሆነ ወላጅ ይከበራል
ጠላትም ያሳፍራል ዜግነት ያኮራል
ሰላም ይዳብራል ድንበር ይከበራል
ታርሶ ይመረታል ሀብት ይበረክታል
በፍቅር በአንድነት ሰቅሶ እንኳን ይደምቃል
እናንተ እንድ ሁኑ እሱ ብቻ ይበቃል
ሶስተኛው አባል እግዚአብሄር ይሆናል
ሁለት ስትሆኑ እገኛሰሁ ብሏል
የጎደሰው ነገር እሱ ያሟዋል!
ፈጣሪ ዕውነት ነው ቃሉን ይጠብቃል።

*!!! ጀግናች ሕያው ናችሁ !!!

ጤና ይስጥልን ሙታን እንዴት ናችሁ ጀግኖች
ዳር ድንበር ተከብሮ ለትውልድ እንዲቆይ
የተሰዋችሁልን እናትና አባቶች
ጋሻ መከታችን ከቶ እንደምን ናችሁ
ለአገር ለወገን መስዋዕት የሆናችሁ
ክቡራት ክቡራን
በሥራችሁ ህያዋን በስጋችሁ ሙታን
አገር ጠብቃችሁ ዳር ድንበር ተከብሮ እዚህ ያደረሳችሁ
የተሰደዳችሁ ሕይወት የገበራችሁ ለአገር የሞታችሁ
በአፍቅሮ ንዋይ በኑሮ ምቾት ያልተዘናጋችሁ
ድሃ ያልበደላችሁ ፍትህ ያላዛባችሁ
በፈሪሀ እግዚአብሔር የተጠመቃችሁ
የኛ እናት አባቶች አያት ቅድመአያቶች፤
ምስጋና ይድረሳችሁ
በመልካም ሥራችሁ እናስታውሳችኋለን
ያወረሳችሁንን ቅርስ እንጠብቃለን
አዎን ትውልድ የማይረሳው ታሪክ የማይሽረው
እስከዘለዓለሙ ስማችሁ ክቡር ነው፤
እናንተ ባትኖሩም ሥራችሁ ህያው ነው !!!!!

<u>አርዓያ ጀግኖች</u>



አፄ ቴዎድሮስ



አፄ ምኒልክ



አፄ ዮሐንሥ



እቴጌ ጣይቱ ብጡል



ራስ አሉላ አባነጋ



አቡነ ጴጥሮስ



ራስ አበበ አረጋይ



ደጃዝማች ዘረዓይ ደረስ



ጠ/ሚ አክሊሉ ሐብተወልድ



ደጃዝማች ሀፂ/ልሀላርያም ሀማሮ



ደጃዝማች በላይ ዘለቀ



ደጃዝማች ገረሱ ዱኪ



ራስ አባተ ቢያለው



ፈታውራሪ ኃብተጊዮርጊስ



ደጃዝማች ባልቻ



ሰምአን አደፍር



ሞገስ አስገዶምና አብርሀ ደቦጭ



ወጣት አርበኞች



እናት አርበኞች



ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድሕን



ሎሬት አርቲስት አፈወርቅ

ወ.ዘ.ተ

*** ግነው አሱ**

ህዝቦች ያፈቅሩታል ዜጎችን ይወዱታል
በቁልቁለት ያቅፋል ዳገት ይደግፋል
በጦርነት ጊዜ፤ አብሮ ይሰለፋል
የሞተ ይቀብራል ከፈን ልብስ ይሆናል
በሠርግ በቀለበት ያደምቃል ያስውባል
ወጣቶች አንደ አምባር በእጅ ያጠልቁታል
ከዚያም አልፎ ተርፎ ቀለበት ይሆናል
የድሜ ባለጸጎች እንገት ላይ ያሰሩታል
ነገሥታት ዙፋን ላይ፤ አብሮ ይቀመጣል
ዘማቾች ተሰፋችን ስንቃችን ይሉታል
የጃማይካ ሰዎች አምላክ ነው ይሉታል
የጣሊያኖች ፋሺስቶች ክሩቅ ይፈሩታል
የእንግሊዝ ሰዎች የጎሪጥ ያዩታል
የጀርመን ናዚዎች በአብዲሳ ያውቁታል
የቱርክ ፓሻዎች ይበሳጩበታል
ጠላት በየጊዜው ድል በማድረግ ረቷል
ሱማሌዎች ሱዳኖች ክንዱን ቀምሰውታል
ብዙ አፍሪካውያን አርማ አድርገውታል
ታጋይ አፍሪካውያን መመኪያ ይሉታል
ዘረዓይ ሮማ ላይ ትእይንት ሰርቶበታል
ምኒልክ አድዋ ላይ ጠላት ረቶበታል
አቴጌ ጣይቱ ቀሚሰ አርገውታል
ከቴዎድሮስ ጋራ መቅደላ አብሮ ወድቋል

ከዮሐንስ ጋራ በመተማ ቆስሏል
ከራሰ አሉላ ጋር ጠላት ድል አድርጓል
ከራስ አበበ ጋር ጣሊያን እርበድብዷል
በላይ ዘለቀን ረድቶ ቀን ተሌሊት ተዋግቷል
ከተፈረ ጋራ አውሮፓ ተሰዷል
ብዙ ጊዜ ወድቆ ሳይሰበር ተነስቷል
ብዙ ጊዜ ቆስሎ ከመሞት አምልጧል
እሰክዛሬ ናፇል ወደፊት ይኖራል
በእንገት ላይ ከራባት በሸማ ላይ ጥለት
በወገብ ላይ መቀነት
ሁሉም የሚያምርበት ሁሉ የሚደነቅለት
ሁሉ የዘፈነለት ሁሉ የዘመረለት
በሃዘን በደስታ ሁሉም ዘንድ የሚገኝ
ሙሽራ የሚቀበል አስከሬን የሚሸኝ
ከፀሃይ ጋር ወጥቶ የሚታይ ከምሰራቅ
ቀን በሙሉ ተጉዞ በማታ የሚጠልቅ
ከሙስሊም ከክርስቲያን ጋር በዓላት የሚያደምቅ
የዓላማ ብርታት የጽናት ምልክት
እሱ ልምላሜ ነው ተስፋና ጀግንነት
እሱ አበሻ ነው እሱ ኢትዮጵያዊነት
የጠይሙ አበሻ የኢትዮጵያዊነት ምልክት
የአምላክ ፈቃድ ሆኖ ፈጽሞ የማይሞት
የክብር አርማችን
ውቡ ባንዲራችን ።

*<u>ለሰላም ለፍቅር</u>

ለሰላም ለፍቅር
ሁሉም ነገር ይቅር
ልብ አድራቂ ጉንፋን መነታረክ ይቅር
ቂም በቀል ይጥፋልን! አርቆ ይለደድ።
በክፉ መተያየት ከኛ ፊት ይወገድ
ዜጎች እንቀራረብ አዎን እንጠያየቅ
በፍቅር ለመኖር ልዩነታችንን በውይይት እናርቅ
ለሳምታችን ይሁን ቅንነት ጨዋነት
በሰምና በወርቅ አሽሙር የሌለበት
ተካፍለን እንብላ ማህበር እንጠጣ
የናት የአባቶቻችን የጥንቱን እናምጣ
ቀን በሥራ ደክመን ማታ እንረፍበት
ለእገር ለወገን ተግተን እንሥራበት
እባትና እናቶች ደካሞች እንጡርበት
ሠላም ባገር ሰፍኖ ሕዝባችን ይደለት
ግልጽ እንጨዋወት እንሰግግ ለሙን
በር እንከፈት እንጂ መዘጋጋት ይቅርብን
እህትና ወንድም የእንድ አገር ዜጎች ነን
ፍቅር እንለዋወጥ ልባችሁ ይውደደን
የእንድ አገር ዜጎች ነን በመዳሞች ነን
እገር መከፋፈል! መካለልን ይቅርብን
ለጋችን ደግችን ልባችን አንድ ይሁን
መጥተን እንጣችሁ መጥታችሁ እትጡን
እንደ አገራችን ባህል ሻይ ቡና እፍሉልን

ስንሰነባበት ዳግም ያገናኘን ደህና ግቡ በሉን
ከቶ ለምንድነው እንዲህ መጠፋፋት
ሰንት ዘመን ስመኖር፤ምን ይጠቅማል ክፋት
ዘንድሮ የት አሉ፤አምና የነበሩ
ብዙዎች አለፉ ሄዱ እየተጠሩ
አኛም በተራችን መጓዛችን ላይቀር
ቁም ነገር እንሥራ ዛሬ እንፋቀር
ከመካከላችን ለሰላም ለፍቅር አልገዛም የሚል
ይመክር ይዘክር ራሱን እንዲያስተካክል
አፈንጋጩ ወገን ራሱን ብቻ የሚወድ
በአንድነት ወቅስነው መንፈስ ቅዱስ ይውረድ
ንስሐ በመግባት አንደ አዲስ ይወለድ
በሰላም በፍቅር ስንለለት ይታሰር
መልካም ዜጋ እንዲሆን የፍቅር አምባሳደር
ያለፈው ይበቃል
በመራራቃችን ጉዳት ደርሶብናል።
ለዜጎች ብልጽግና ለአገራችን ዕድገት
በሕብረት ተነስተን ተግተን እንሥራበት

*<u>ቀን ግታ ገዳይ</u>
ባሰጊዜ አበባ
አምራና ተውባ
ፍጥረት ለመማረክ
በፍቅር ለማብረክረክ
ንቅሳት ተነቅሳ

የክት ልብሷን ለብሳ
ሽቶ ተቀብታ
በየአቅጣጫው ረጭታ
ቀንበጣም አንቡጣም
ውበታም ድምቀቷም
ባለይኗ ትጠቅሳለች
ክሩቅ ትጣራለች
ኑ አዩኝ ትላለች
ልብ ታማልላለች
ሰው ሁሉ አያልፋትም
አይቶም አይጠግባትም
አተኩሮ ያያታል
ውበቷን ያደንቃል
ልቡ ይሸበራል
በፍቅሯ ይማረካል
ቆም ብሎ ያያታል
በጄ ይነካታል
በአፍንጫው ያሽታታል
በሰሜት ተውጦ
ይወለዳታል ቆርጦ
የሱ ያደርጋታል
ኪሱ ይክታታል
ጥቂትም ሳይዘገይ ሥራ ትጀምራለች
የቀጣፊዋን እጅ ታሳክከዋለች
አካል ሰውነቱ ውሃ እየቋጠረ

መላው ሰውነቱ ያባብጥ ጀመረ
ያቺ ውብ እበባ ለካሰ መርዝ ኖራለች
ልክ እንደ በሰሰ ፍሬ፤ ሰውን የምታሳስት፤ መልክ
እያሳመረች
ከጠዋት እስከማታ ውበቷን ተጠቅማ ሰመጉዳት የቆመች
ያ ሁሉ ጥረት ውበትና ብልጠት
ለካሰ ወጥመድ ኖሯል ፍጥረትን ለመጉዳት
እሱ በየሥፍራው በሰማይ በምድር
በእየር በባሕር
ከሔዋን ከእዳም ልጆች
ከዱር እንማቶች ከወፎች ከእማዎች
ሽር ጉድ እያሉ
መረብ የሚጥሉ
ወጥመድ የሚሰሩ
ተንኮል የሚያደሩ
እጥፍቶ ሰመጥፋት ተግተው የሚሰሩ
ራሳቸው ሞተው ፍጥረት የሚገድሉ
ክፉ የሚያስደሰታቸው የሰይጣን ፈረሶች
ቀን ማታ ገዳዮች

*<u>የኋላ የኋላ መፈንዳቱ አይቀርም</u>

በብሌኑ እይናችን እይተን እንዳላየን
በሁለቱ ጆሮዋችን ሰምተን እንዳልሰማን
ግታ በሕልማችን ቀንም በውናችን
ያየን የሰማነውን ማመን እያቃተ
ማሰተዋል ተስኖን ይኸው እዚህ ደረስን

የልባችን መድማት ያካላችን ጉዳት በተግባር እያየን
ይኸው እዚህ ደረስን
ዛሬም ቢሆን ያው ነን
ያላደገች እናት በችግር ውስጥ ቆማ
ሰቅሶና ዋይታዋ ድምጿ እየተለማ
የህዝባችን ስደት ባይናችን እያየን
በደቡብ አፍሪካ በእሳት የነደዱት እጥንት እያሸተትን
ያቅማችን ማዋጣት መልካም መስራት ጠልተን
እገር እንደዳበ ቆርሰን እየሰጠን
በራሳችን ችግር ቆመን እየሳቅን
መልካም ነገር መስሎን እንደሰታለን
የኛ ተራ ደርሶ በራችን ሲንኳኳ ለደት እንመርጣለን
ካሰብነው ሳንደርሰ መንገድ እንሞታለን
ጎበዝ ማሰተዋል ካቃተን፤ እንዲህ ያለ ችገር
ጤና መሆናችንን ራሳችን እንመርምር
በችላ ባይነት ያሳደግነው ፍዳ
እያደገ ይመጣል ያልከፈልነው ዕዳ
ነገሩ ተቀብሮ ሰጊዜው ቢቆይም
የኋላ የኋላ መፈንዳቱ እይቀርም

**<u>ለጉበኛው</u>

ተጠየቅ ባለ ጊዜ ባለ ብዙ ሰዓት
እንዳሻህ የምትኖረው የሌለብህ ፍርሀት
በእድልዎ በጉቦ ተሸፍነህ ያለህ
ፖሊስ የማይዝህ ዳኛ የማይቀጣህ
እግዚአብሄር ዝም ያለህ
የዘመኑ ጀግና ጊዜ ያበቀለህ
ተራራ ነኝ ባዩ ዘመን የከመረህ ጊዜ ያረዘመህ
ልብህ የደደረው ሞት የማይታይህ

ሰው መሆንህን የረሳህ የምትሞት የማይመስልህ
እኛማ እኛ ነን በአድልዎህ የቆሰልን
ከአንድ እናት ተወልደን በገንዘብ የሸጥከን
ጊዜ ስለሰጠህ ዛሬ የምትበድለን
በሥራህ የታመምን ከሞቱት ያልተሻልን
ጉድጓድ የከተትከን ብዙ ሰዎች እለን
በተፈጥሮ ሳይሆን ያንተ ሰለባ ነን
ከታች ሆነን መደላይ ድምጽ እናሰማለን
ፍትሕ እሰከምናገኝ እቤት እንላለን
የበደልህ ብዛት ደመረን እባዝተን
የምትመጣበትን፡ ቀን እንጠብቃለን
ፍርድ እንጠይቃለን
የዘረፍከው ንብረ የቀጠፍከው ሕይወት
የሠራኸው ህጢአቶች እዳዎችህ ናቸው
እጥፍ ድርብ አድርገህ ነገ የምትከፍላቸው
የወንጀልህ ብዛት በመዝገብ ውስጥ ሰፍሯል
ጊዜው ሩቅ ቢመስልም
ፍርድ ቤት መቅረብህI ቅጣትህ አይቀርም
ተገፍተን የተጣልን በእድልዎ ያለቅን
ፍትህ ርትዕ ያጣን
ጥቂት እንዳንመስልህ በቁጥር ብዙ ነን
እንፋረዳለን
ከሳሽህ እኛ ነን እንተ ተከሳሽ
ወቅትህ እንዲህ ሲያልፍ ቀንህ እንዲያ ሲመሽ
ዶሴ ተከፍቶልህA፡ቀጠሮህ ተዳርሷልI
መጥሪያ ይደርሰህAI
ዳኛ ተሰይሟል ፍርድ ይጠብቅሃA
ባጠፋኸው መጠን ይፈረድብሃA

***ምነው ድሮ በኖርኩ

ምነው ቀድሞ በኖርኩ ያኔ እንዳማረብን
የሕዝብ ጀግንነት የዜጎች ማንነት ሳይለወጥብን
እንደተከበረ ያገሬ ዳር ድንበር
ከጎንዋ ሳትሳሳ ከቁመትዋ ሳታጥር
የእናቴ ፊት ሳይጠቁር
የህዝቤ እንድነት በዘር ሳይከፋፈል
እርስ በእርስ መካሰስ ባገሬ ላይ ሳይበቅል
በጎሳ ፖለቲካ ሳትመሰቃቀል
ባላሬ እግዳሚ እገር ሳትከጀል
ሰው ሃፍረቱን ሳይገልጥ ሰው ሙሌነት ሳይወድ
በራስ ወዳድነት ጨርቁን ጥሎ ሳይሄድ
እጭበርብሮ ሰርቆ ማትረፍ ሳይለመድ
ክፉ ነገር መሥራት እንዲህ ሳይወደድ
ኩሩ ዜግነት የእንድነት ፍቅር እንደዚህ ሳይወርዱ
ይሉኝታና ክብር ካገር ሳይሰደዱ
የእገር መውደድ ስሜት የባንዲራ ክብር እርቀው ሳይሄዱ
የእፍሪካ ዳቦ ቅርጫት ተብሎ እንደነበር
የአገር የሕዝብ ክብር እብዮ እንደነበር
ጠላት ተመልሶ እገሬን ሳይረግጣት
ሀሳቡ ተሳክቶ እግር እንገቷን ሳይቆርጣት
ሁሉም እገር ሳይቀድመን
ከኋላችን መጥቶ ሮጦ ሳያመልጠን
ትውልድ ራሱን ሳይወድ ሰዉ ራሱን ሳይመርጥ
ሀላፊነት ረስቶ እንዲህ ሳይለወጥ

በራስ ወዳድነት በጎሳ ማጥ ሳይሰምጥ
በዓለማችን ዙርያ እንደጉንዳን ሳንፈስ
አበሻነት ወርዶ እንደአሁኑ ሳይረክስ
የኢትዮጵያዬ ከብር እንደዚህ ሳይቀንስ
በንዴት ብስጭት አገሬ ሳትከሳ
በህይወት እያለሁ ከአንገቷ ተገምሳ
ከቁመቷ ሳታጥር ከጎኗ ሳትሳሳ
ሰብቻዬ የሚሉት በራስ መውደድ ጣጣ
የግሌን ልወስን ልገንጠል ሳይመጣ
በውርስ ያገኘሁት ክብሬን እንደጠበኩኝ
ምነው ድሮ በኖርኩ እንዲያ እንዳማረብኝ
ጀግኖች አባቶቼ እርቀው ሳይሄዱ በክብር እንዲሸኙኝ
በትውልድ ሰፈሬ ባገሬ እንዲቀብሩኝ

<u>ትዝ አለኝ አገሬ</u>

ትዝ አለኝ አገሬ መስከረም ሲጠባ
ሳር ቅጠሉ ተውቦ በአበባ
አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ሁሉም ነገር ሰምሰም
ተራራ ሸንተረሩ በአበቦች ቀለም
ባሕር ጣልቃ ገብቶ ተራራ ቢከልሰኝም
የአገሬ በዓላት የአገሬ ድግሶች ከቶ አይረሱኝም
ወርሀ ፈንጠዝያ መልበሻ ግጌጫ
የክረምቱ ወራት ተጠራርጎ መውጫ
ጨዋታ ግርግር ሆያሆዬ ሰምሰም
ሀሳቤን ወሰዱት የለሁም የለሁም

የአገር ፍቅር ስሜት የሕዝቤ ትውስታ
ውስጤን አሸፈተው በሀሳብ ተንገላታ

<u>*** ካገሩ የወጣ አገሩ እስኪመስስ ...</u>

ሁሉም በቦታው እያለ ከኢትዮጵያ ሳይጠፉ
ነገር ተውገርግሮ መሰደድ ተሰፋፉ
ገበሬ ነጋዴ መንግሥት ሰራተኛው
ከአገር ስመኮብለል ጉቦ የማይከፍል
ዲቪ የማይሞላ ቪዛ የማይገዛ ከቶ ማን ይገኛል
እንደ አሰግችን እኛም ተሸከረከርን
አቅጣጫ ሳንመርጥ ሁሉ አገር አዳረስን
ሰው እንዳይሆን የለም ብዙ ነገር አየን
ከገዳያችን ጋር ከጣሊያን ታረቅን
ሮማ ብርቅ ሆኖብን መጠለያ ጠየቅን
ፊደላችን ጠልተን ላቲንኛ መረጥን
የእንግሊዝ የጣሊያን ዜግነት ተቀበልን
ከአዲስ አበባ ይልቅ ሎንዶንን አደነቅን
የቴዎድሮስ ገዳይ የጉብርዬ ገዳይ እንግሊዝን ወደድን
ወዳጅ ጠላት ሳይቀር ሁሉም ተሰግመጥን
ድሀ ሀብታም ሳንል ከተገኘው አገር
ከቅርብ ጎረቤቶች ከምስኪኗ አፍሪካ
መካከለኛው ምስራቅ አውሮፓ አሜሪካ
ሞስኮብ ካናዳ አውስትራሊያ
ቻይና እስያ
ሱማሌ ጅቡቲ ሱዳንና ኬኒያ

እንደ አውሎ ነፋስ ሁሉም በታ ደርሰን
ሰያይነቱ አየን ሁሉም ነገር ቀመሰን
ያልረገጥነው የሰም የምድር መልክዓ
ምድር
ችግር ተለማመድን፤ ሁሉም ተሰማመጥን
ኢትዮጵያዊነትን አበሻነት ሰወጥን
የወዳጅ ጠላት ሳይቀር
እግዜር ከፈጠረው ከዘረጋው አገር
የማናውቀው የለም ያልረገጥነው ምድር
ሕይወት ከታየበት አስትንፋስ ካለበት
ከቶም አይገኝም እኛ ያልደረሰንበት
እግማ ኢትዮጵያ ከአንቺ ከተሰየን
ሰው አንደግይሆን የሰም ብዙ ነገር አየን
አሉን ትዝታዎች
አያሌ ትዝብቶች
የሰው ልጅ አይነቱን የአዳም ልጅ ፀባዩን
ባሕልና ወጉን ዕምነት ሀይማኖቱን
መልክና ቀሰሙን ጥቁርና ነጩን
ቀጫጫ ወፍራሙን
በግና ፍየሉን የዋሕ መሰሪውን
ወንድ የሆነች ሴቷን ሴት የሆነ ወንዱን
እግዜር የፈጠረው አካል ሰዋዋጩን
የውሸት ፈገግታ አርቲፊሻል ሳቁን
ታጣሬ ምላሱን ደግና ጨካኙን
የናጠጠ ሀብታም መንገድ ዳር ለማኙን

በካርቶን ላይ ጽፎ ተመጽውቱኝ ባዩን
የሰው አመል አይነት ክፉውና ደጉን
የባህርያት አይነት አሳማና ጅቡን
ዝሆንና ድቡን።
በእጽና በሱሰ የናወዘ ፀባይ
ያለ ምንም ምክንያት ሰው ተኩሶ ገዳይ
ይኸ ሁሉ ሲሆን
በወከባው ዓለም፤ ቀን ተሌሊት ሮጠን
ዳገት ቁልቁለቱን ጥርሳችንን ነክሰን
የቀን እረፍት አጥተን ግታ ዕንቅልፍ ናፍቆን
ያጋጠመን ጣጣ በሆዳችን ችሰን
ከልኩ ሲያልፍብን ወደ ውስጥ አልቅሰን
በየደረሰንበት ሁሉም ነገር አይተን
ሁሉም ችግር ችሰን ይኸው እዚህ ደረስን
እግዚአብሄር ይመስገን
ካገሩ የወጣ አገሩ አሰኪመስሰ
ቢጭኑት አሕያ ቢጋልቡት ፈረስ

<u>እንከርዳድ ከሰንዴ</u>

በዋዛ ፈዛዛ በከንቱ ሰጠፉው
ሰባከነው ዘመን ተጠያቂው ማነው
እኔስ ይመስለኛል ተከሳሽ ነን እኛ
እያሻም ጠበቃ አይጠቅመንም ዳኛ
በዕድሜ በሰሰናል
ጎልማሳውን አልፈን አዛውንት ሆነናል

ትምሕርት ቀስመናል በልምድ ጎልብተናል
በየሃይማኖታችን የእግዜር ቃል ሰምተናል
በእገርም ተወልደን ብዙ ዓመት ኖረናል
እቀበት ቁልቁሰት ወጥተናል ወርደናል
ዘውድ እገዛዘና የምሰራቅ የምዕራብ ርእዮት ቀምሰናል
ባህር እቆራርጠን ሌላ እገር ደርሰናል
ከብዙ ዘር እይነት ተካፍሰን በልተናል
ይኽ ሁሉ ሆነን ከዚህ ሁሉ ደርሰን
ታዲያ ለምን ይሆን እንደዚህ የምንሆን
እንከርዳድ ከስንዴ መለየት ያቃተን?

<u>መቼ ተግርን</u>

ዛሬስ ቢሆን መቼ ተግርን
ስህተታችንን መቼ እረምን
እርቀ ሰላም መቼ እወረድን
ከመጎዳዳት መች ተቆጠብን
እርስ በእርሳችን መች ተፋቀርን
ወደ እንድነት መቼ መጣን
ስሰሠላም መቼ እወራን
ሕሊናችንን መች እፀዳን
እመላችንን መቼ ገራን
ከራስ ማፍቀር መቼ ተቆጠብን
እርስ በርሳችን መች ተግባባን
መነቃቀፍ መነቋቆር መቼ እቆምን
ከችግሮች መቼ ተማርን

<u>*ውቧ እናት</u>

ግነው ሰምሽ
የግን ቆንጆ የግን ውብ ነሽ
ሰላም ፍቅር ተስፋ ምስልሽ
እረንጓዴ ቢጫ ቀይ እርግሽ
ልዑል እግዚእብሄር የሰየመሽ
በመጽሐፉ ያወደሰሽ በእንደበቱ የዘከረሽ
ጽላቱና መስቀሉን ያለፈርግ ያሰረከበሽ
ከእገር በላይ የመረጠሽ
በፀሎት ብርታት ውሰሽ ያደርሽ
ብዙ እርግዘሽ ጥቂት የወሰድሽ
ደም ገብረሽ ልጅ ያሳደግሽ
ጠላት ከቦሽ ሁሌ ታመሽ እንቅልፍ ያጣሽ
ሰው ገብረሽ እዚህ የደረስሽ
በሰቆቃ በሐዘን ያለሽ
ጥንትም ዛሬም በዓለም ዙርያ ትኩረት የሳብሽ
የሚመኙሽ ልብ የሰረቅሽ ህዝብ ያማለልሽ
በተአምር በቸር የኖርሽ
ጥርስ ተነክሶብሽ በእግዜር ፈቃድ ውለሽ ያደርሽ
ከዳር ደርሰሽ በቋፍ ያለሽ
ዝንተ ዓለም መስዋዕትነት
በትጥቅ ትግል በጦርነት
ልጅ ገብረሽ ንጉሥ ከፍለሽ
ድፍን ዜጋ ጥሎሽ ጥለሽ
ተፈርዶብሽ በመለኮት በቸር ያለሽ
ለምን ይሆን እንዲህ ተግተው የሚያልሙብሽ
ሰላይ ልከው የሚያጠኑሽ
ወደኋላ የሚሰቡሽ
ሳንሻ ስለው የሚቆርጡሽ

ጭረው ቧጠው የሚያቆስሉሽ የሚያደሙሽ
ስብቀው አሳብቀው የሚያጣሉሽ
ምክንያት ፈጥረው የሚወሩሽ

<u>ፖለቲካ መብት ነው</u>

ፖለቲካ መብት ነው መብትም ፖለቲካ
የሰው ልጅ ጥቅሙ በብቱ እንዳይነካ
አግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠው ነጻነት
በምንም በማንም እንዳይነጠቅበት
ታግሎ ተከራክሮ ማለከበር አለበት
ጠበቃ ሆኖ በመከራከር
ወታደር ሆኖ በማለከበር
ዝምተኛው ውኃ እንኩዋን ሲመታ በድንጋይ
ሲገፋ ሲነካ ይናገር የለም ወይ
አግዚአብሔር የሰጠን መብትና ነጻነት
የለአንዳች ገደብ መከበር አለበት
ሞትማ አንደዜ ነው መቼ ይደገማል
በቁም መቀበር ግን ከሁሉም ይከፋል
የትንሽ ዛፍ ፍሬ ወድቆ እንዲበቅል ጊዜ ከተሰጠው
መገርሰስ የሚያቅተው ሥሩ ሲደራጅ ነው
በዝምታ በይሉኝታ ጀምበር ከጠለቀ
ማረም አይቻልም አለቀ ደቀቀ

<u>*የፈሰሰ ውኃ</u>

አንዳንዶቻችንማ አጀንዳ አየለቀቅን

ድሮ የሆነውን ከአሁን እየደባለቅን
ይርጋ ሳያግደን እንፈተፍታለን
ለማዘናጋት ይሁን ነገር ለማልከሰከስ
እንከብ እንከብና በነገር ግን ማፍረስ
ወደኋላ መሄድ መናድ እንወዳለን
የደረቀ ቁስል አከን እናደማለን
አጥንት እየቆጠርን ሐረግ እንመዛለን
ታሪክ እያጣመምን ቀለም እንቀባለን
መልስ የሌለው ጥያቄ ዛሬ እንጠይቃለን
በጭቅጭቅ ንትርክ ጊዜ እንገድላለን
መቋጫ እንዳይኖር አጀንዳ አሳክነን እንበተናለን
ያለፉት ጥፋቶች ለመማሪያ ወለደን ለታሪክ አኑረን
ለነገው ጉዞአችን አላማችን አውቀን
በወቅቱ ችግሮቻችን ቁርጥ አቋም ጨብጠን
ወደፊት እንጓዝ አንደ አንድ ሰው ሆነን
የሞተውም ሞቷል ተውት ይረፍበት
ወደ ኋላ አንሂድ ጠንቅ ነው ለዕድገት
ራሶች፤ደጃዝማቾች ንጉሶችን መውቀስ
ከመቃብር ገብቶ ምስጥ የበላውን መክሰስ
ወደኋላ መጓዝ ከነፋስ ጋር መንፈስ
አዘናጊ መፈክር የፈሰሰ ማፈስ

<u>መሬት ያራሹ ነው</u>

የአገሬ ገበሬ እንደምን ከርመሀል
እንዴት ለንብተሀል

እመቱ ወዴት ነው
ጉልበቱ፣ ጥናቱ፣ ዘመኑ እንዴት ነው
እንዴት ነው ባላገር እደምን ነው እርሻው
ቡታያው የት ደርሷል አብሏል አፍርቷል?
እንደቀድሞ ዘመን መሬቱ ስምልሟል
ልጆች ቦርቀዋል በዓመት በዓል ዘፍነዋል
ሙልሙልና እንጎቻ ስጦታ አግኝተዋል
ቁጠማና እበባ ፍቅር ተስዋውጠዋል
በአዲሱ ዘመን አዲስ ልብስ ገዝተዋል
በከረምቱ ውሀ ተራጭተው አልፈዋል
ዛሬ ምን መስሰዋል?
የወተት ላሞችህ ጠቦት ፍየሎችህ
በጎች ግመሎችህ
ጎጆና ጎተራህ
እትፍራ ተናገር በድፍረት አስረዳ
መሬት ያራሹ ነው ያበጠው ይፈንዳ

<u>የኛ ድርሻ</u>

ተፈጥሮ ሲከፋ እግዚአብሄር ሲጨክን
ወገን በውሀ ጥም በረሀብ ሲማስን
ደመናና ዝናብ ሲጠፉ ከአገር
የማይገኝ ሆኖ በወግ አንኳን መቀበር
ውሀ ምግብ ፍሰጋ የወጣ እዚያው ሲቀር
ልብ እንዴት ይጨክን በአገር በሕዝብ ችግር
እንዴት እንሰማም ወሬ አንጠያይቅም

አገርና ሕዝብ፣ እንዴት እንዳደሩ፣ ስማቅ እንጥርም
ምንም ባገር ባንሆን፣ ይመስከተናል
ዓለም ሁሉ አውቆታል፣ ወሬው እንደሁ ተዳርሷአል
ንቁ የሆነ ዜጋ ከሆዱ ቀንሶ ድርሻውን አዋጥቷል
የታለ ያንተ ፋንታ፣ የኛ ድርሻ የታል?
ድርቅና ረሀብ መች ጊዜ ይስጣል

<u>የአበሻ ልጇ</u>

ባንዲራ ነው ስሜ ኢትዮጵያ ነው ቃሌ
ያሉትን ይበሉ አሱ ነው አመሌ
እሱ ነው የኔ ሱስ ነው አሷም የኔ ነፍስ
ቃሌን አስውጥም አስከሞቴ ድረስ
ከመሬት ላይ ስድህ ገና በጨቅላነት
ከጡጦ ከእንጎቻ ጋር አብሬ የጠባኋት
ዛሬ ራሴን ስችል እልችልም ልከዳት
የስው ፊት እይቼ ነውር ነው ብከዳት
ሌላ ቋንቋ የሰኝም የኔ እናት እሷ ናት
እኔ ማስት ይህ ነኝ
በጥቁረቴ የማምን አበሻው ልጇ ነኝ

<u>*ኢትዮጵያ የኛ ናት</u>

ቁጠር የጀግና አይነት እያት ቅድመ እያትህ
ቅርስህን አላየው እከሱም ጎንደር ወስደህ፣
የሱሲ መገኛ እውሳን እስትብችተህ፣
ዳርና ድንበራችን በስሜን በደቡብ
በምሥራቅ በምዕራብ
ዶጋሊ፣ እድዋ መተማ የድል ቦታዎችህ፣

ግሰረጃ አሳይተህ ሸልሰህ ፎክረህ፣
እንደ አርበኞቹ፣ ፀጉርህን አንፍረህ፣ ኧረ ጎራው ብለህ
አንበሳ፣ ግስላ፣ እንስት ነብር መስለህ።
ይሰማ እንደሁ ይሰማ አውነት አይካድም፣
በዶላር ከሆነ አንደራደርም፣
ሀብት ይሄዳል ይመጣል አንከራከርም፣
ታሪክ ግን ቋሚ ነው አይነቃነቅም፣
አውነት የማዜር ልጅ ነው ሥፍራውን አይለቅም፣
የሰውም አንሻም የኛንም አንሰቅም፣
ኢትዮጵያ የኛ ናት ለማንም አንሰጥም ።

<u>መድሃኒት እንቀምም</u>
አስቲ መላ ምቱ ጊዜው ተበላሽቷል
አረም ከሰብል ተጋፍቶ ይበቅላል
ልብ የሚነቅል ሳል ትክ ትክ ተዛምቷል
ገንዘብ ትበላሽቶ ሰውን አበላሽቷል
ቆሽት የሚያቃጥል የሚያበግን በዝቷል
ችግሩን ለማጥፋት በአንድነት እንትመም
ከመሞት ሰመዳን መድሃኒት እንቀምም

<u>አያድርስ</u>
ፈኖና አፉፋ አንድ ነው ሥራቸው
ባየር የሚሞሉ ባዶ ነው ውስጣቸው
ስልቻም ቀልቀሎ ቀልቀሎም ስልቻ
ተግባራቸው ያው ነው ነፋስ ማከማቻ
የተፈጠሩበት ሥራ ተግባራቸው
የተሞሉበትን ጎስሮ ማኖር ነው
ሆዳቸውም ይሁን ውስጣቸው ሲጎድል

በመንፈያ እየነፉ መሙላት ያስፈልጋል
ይሽው ነው ሥራቸው
ከርሳቸው መሙላት ነው
እነሱን የሚመስሉ
ብዙ ፍጥረታት አሉ
የኔ ነው የሚሉት አቋም የሌላቸው
የተሞሉትን መሆን፣ የሆነ ሥራቸው
ከአፉፋና ፈኖ ምንም የማይሻሉ
እንደሰዓት ተሞልተው የሚኖሩ አሉ

<u>*ደርጎች</u>
አገሬ ኢትዮጵያ የባዘኑች አገር
ሩሲያ ተጓዘች፣ ርእዮት ልትበደር
ወቅታቸው ጊዜአቸው አጣቸው ሆነና
ቻይና፣ ኮሪያ፣ ኩባ፣ ሄድን፣ ደጅ ልትጠና
አገር የሚመሩ ሰው ወለሉ ቢሉን
በትምህርት የላቁ በልምድ የዳበሩ ምሁራንን ትተን
በተቃራኒው ሄደን ተንኮለኞች መረጥን
ጠመንጃ የያዙ ጮሌዎችን ተከልን
የኋላ የኋላ ፊታቸውን አዙረው በኛው ተኮሱብን
ከሰልሳ ጀምሮ መቁጠር እስኪያቅተን
የዘራነውን አጨድን ያጨድነውን ከመርን
17 ዓመት በጠግግ ማጭድ በብረት መደሻ
አንድ ትውልድ ረገፈ አሰቀ አበሻ
የፓርቲ ጋጋታ የገዳይ ግርገር
ዘወትር ማጓራት ጉራና መፈከር
ባዶ አስቀርተውን ኮበለሉ ከአገር

በራሺያ ጥይት አረሱ ግዛቶች
ገደሉ ሚኒስትሮች፤ ጨረሱ ጄኔራሎች
ነጋዴ ገበሬ ተማሪ እስተማሪዎች
አገር ባዶ አድርገው ጥሰው ኮበለሉ
በአየር በምድር ሸሽተው እግሬን አውጭኝ አሉ
ካድሬ ወታደሮች እነዚያ ብኩኖች
እጓርተው ፈከረው የሾለኩ ፈሪዮች
ሰው በላ፤ ሰው ፈጆች፤ አውሬ የቀን ጅቦች
ጨካኝ እረመኔ ስልጡን ነፍሰ ገዳዮች
ፍየል እነሱ ሆነው በፍየል እየመሰሉ
ተኩሳና ቀበሮ ሆነው፤ የአንድ ወቅት ትውልድ በሉ
እኒያ ይሉኝታ ቢሶች፤ የፕሮፓጋንዳ ካድሬዎች
የሰው ሥጋ በልተው የፍየል ወጠጤ ዘፋኞች
አንድ ቀን ሰንኳ ዕውነት ሳይናገሩ
የፍየል ወጠጤ ብለው እንደጨፈሩ
ሁሉ እንደዋሹን እንዳደነጋገሩ
በጠራራ ፀሐይ ተበትነው ቀሩ
አንድ ሰው አንድ ጥይት እስቲቀር እንሞታሰን ብለው
ሲያጓሩ ከርመው ሲፈከሩ ኖረው
ከሕዝብ ተደብቀው በምድር ባየር ሾልከው
በጠራራ ፀሀይ እግሬን አውጪኝ አሉ ድንበር
አቆራርጠው
ያኘኩትን ሳይውጡ ተበተኑ ተነው
እሥራ ሰባት ዓመት ሁሉ እንዳጓሩ፤
እንደቀባጠሩ ውሸት እንዳወሩ
መጨረሻቸው ሳያምር ተበትነው ቀሩ
በሰፈሩት ቁና በገነቡት እሰር ቤት፤ ተራቸው ታሰሩ
<u>ከደርግ ዘመን ግሰታወሻዎች የተቀነጨበ</u>

"የደርግ የመከራና የስቆታ ዓመታት ..(በጉራጌ ቾሃ) የወጣት ሬሳ በየእደባባዩ፤በየገበያው፤ በየንዳናው ተጣለ ደማቸው እንደንርፍ ወረደ፤ የረጋው ደምም ውሻ በላው፤ እናቶች የልጆቻቸን ሬሳ እርቃኑን ተንጋሎ ከወደቀበት ሆድ ሆዱን በእግሮቻቸው ተመላለለው እየረገጡ በሰልፍ እንዲያልፉ ታዘዙ። ዘመድ እዝማድ የሆነውም ተመሳሳይ ድርጊት እንዲፈጽም ተገደደ ። የልጆቻቸው ሬሳ እርግጫ በዝቶበት የሆድ ዕቃው በሬንጢጣ በኩል እየተፈተለከ ሲወጣ እያዩ በግድ እልል እንዲሉ እንጂ ስለ ልጆቻቸው እንዳያለቅሱ ተከለከሉ። የወላጅ እንጀት እይችልምና እንባ የተናነቃቸው እናቶች በሽመል ከዘራ ተነረቱ፤ በጠማሽ ሰደፍ ተደቆሱ፤ ተንጋሎ በወድቀ ሬሳ ሳይ ተገፍትረው የተጣሉ እናቶች በዚሁ አጋጣሚ እጅግ ለስከፉ ሽታ ቢኖረውም የልጆቻቸውን ሬሳ ስጃቸው ስመዳሰስና ስመሳም የታደሉ እልታጡም በዚህም የግዚእብሔር ቃል ተፈጸመ ተባለ ትንቢተ ሕዝቅኤል 30:1-9 ...ትንቢተ ሶፎንያስ 2፤3፤12፤ 3-6. 8፤" ከደራሲ ዓለማየሁ ነሪ ኧሰት የተበኘ መጽሓፍ ገጽ 76 እና 77 የተወሰደ

<u>*ሳቄን ገደሉብኝ</u>
ነበር ልበል እንጂ ነበርን አምን ነበርን
ትዝታዎች ያሉን እብረን ብዙ የተጓዝን
ከልጅነት እስከ እውቀት ጓደኞች የነበርን
ስው በላዎች ቀሙኝ
ጓደኞቼ ገድለው ጓደኛ አሳጡኝ
ደስታዬንም ወስደው ሀዘን አሸከሙኝ
የትዝታ ጨዋታ ሳቄንም ገደሉብኝ
ከጓደኞቼ ጋር፤የነበረን ጊዜ፤ሁሉ ትዝ ይለኛል፤
የሃሳብ ጥቁር ፈረስ ድንገት ይወስደኛል
እኒያ ስው በላዎች ያወረዱት መዓት ጎልቶ ይታየኛል
በየ እስር ቤቱ የሞቱ ወጣቶች ተማሪ እስተማሪዎች
ነጋዴዎች፤ ገበሬዎች፤ ወታደሮችና የመንግሥት
ሠራተኞች፤

በውድቅት ጨለማ ከየ አስር ቤቱ እያግበሰበሱ
በጅምላ ሰው ፈጁ አንድ ትውልድ ጨረሱ
የሰቆቃ መአልት የመከራ ሌሊት

(ገዳዮች በአንድ ቀን ሌሊት እየተመላለሱ ሦስቱ ልጆቻቸውን በሙሉ ተራ በተራ በመውሰድ ገድለው ጨርሰውባቸው ብቻቸውን የቀሩ አንድ እናት ከተናገሩት የተወሰደና ምንም ያልተጋነነ እነጋገር)

ቀበሌ ከፍተኛ ማእከላዊ እስር ቤት
የሰው መበለቻ ነበሩ ጣረ ሞት
እኒያ ሰው በላዎች፣ ሳቄን የወሰዱብኝ
ጓደኞቼን ገድለው ደስታ አላጡኝ
ከአብሮ አደጎቼ ጋር ገጠመኞቻችን የሚያውቅ
የጥንቱን አንሰቼ ዛሬ ከማን ልሳቅ
እኒያ ጓደኞቼ እኒያ ወንድሞቼ ሁሌ ትዝ ይሉኛል
ወደ ነበርንበት ቦታ ይስቡኛል
ትዝ ባሉኝ ቁጥር የደስታዬን ቦታ ሃዘን ይመስደዋል
ሙሉ ሳቅ የለኝም ልቤ ዛሬም ይደማል
በግፍ በመገደላቸው አይኔ ዛሬም ያነባል
በሕልሜም በውኔ ሰርክ ይታዩኛል
ጊዜው ሩቅ ቢሆንም ዛሬ ይመስለኛል
ደርግ የረሸናቸው
ቀይ ሽብር የበላቸው
የአገር ተቆርቋሪዎች
አሉ ብዙ ሰዎች
ወረቀት ሰላነበቡ፣ በሞት የተቀጡ የሞህ የአገር ዜጎች
እዚህ አብረን ብንደርስ ዛሬ አብረን ብንኖር
ያለፉትን ዘመናት ትዝታ በመቁጠር

በሚያስቀው አየሳቅን ብዙ እንሠራ ነበር

በአብዮቱ ዘመን አሽሙሮች
መግደል መምታቱ
እንደመንግሱቱ
ተው ቻለው፣ተው ቻለው ሆዴ
ተወዲል ጨፍና ስንዴ
ሩዙን ብላው በዘዴ
ሩዙም ሩዝ ነው ስንዴውም ስንዴ ነው
እኔሰ የገረመኝ ጥቁሩ ስኳር ነው
(ሕዝቡ ከኩባ በእርዳታ የመጣውን ቡናማ ስኳር የነቀፈበት ስንኝ)
የኢትዮጵያ አብዮት ሄደ ገሰገሰ
በአሰረኛ ዓመቱ ጥበቆ ሰበሰ
(ሕዝቡ የደርግ ዘመን የቻይና ቅኝ ይነርሰውን የነቀፈበት ስንኝ)
አለባበስ እንደ ወግ ደረስ (ፍ.ሥ)
ሽር ጉድ በባዶ ሜዳ እንደ ፍሥሐ ገዳ
ቮልቮ ሰደርግ እባል ላዳ ላታጣሪ
እኛ የተረፈን የናት እገር ጥሪ
ወታደራዊው ደርግ ውስታ ዋስልኝ
መኪናውን ወስዶ ባሌን መስበልኝ
(ባለሥልጣኖች በቮሬር እንዲንቀሳቀሱ ተመስኖ በጊዜ ቤት ስለሚገው ሚስቶች ደስ ብሏቸው የጠሙት)
በቅኔ በአሽሙር ስዘፈን ተርቶ
ደርጉን ገዘገዘ በፐሮፓጋንዳ ወግቶ
ከሰሩ መንግሱ እሾሕን በእሾህ ወግቶ
እየዐረበረ፣ እየሰረሰረ
ከነ ግጭድ መዶሻው ደርግን አባረረ

አድዋ ዛሬ ቢሆን

ብዙ ዘመን ሳይሆን የዛሬ መቶ ሃያ አመት
ድል የኛ ነበር በአድዋ ጦርነት
ድል የኛ ነበር በዶጋሊ ጦርነት
የጠላት ጆሮ አይስማ እንዲያው ዛሬ ቢሆን
ጣልያንና እንግሊዝ ታጥቀው ቢመጡብን
ሱዳንና ግብጻውያን ጦር ቢሰብቁብን
ምን ይውጠን ኖሯል ኑ ግጠሙን ቢሉን
ዛሬ ይገኛል ወይ የጥንቱ ጀግንነት
ወኔውስ አለወይ ሕብረትና አንድነት
በፀር ተከፋፍሰን ግድግዳ ግንብ ሰርተን
መግባባት አቅቶን ሰየብቻ ቆመን
በዘር በሀይማኖት እንዲያ ተሸንሽነን
አሰራ ሰባት ቦታ ተካፍለን ተከፍለን
ኤርትራን ሸኝተን እንዲህ ተዝረክርከን
ምን ይውጠን ኖሯል አድዋ ዛሬ ቢሆን?

ነጋዴዎች

ባህር አንዳልነበረን
ጅረት አንዳልበዛብን
ሃይቅ አንዳልተረፈን
ሁሉንም አሰወድደው
በሶም በሁዳዴ አሳነሱን ምነው

****እናቴን ስፈልግ**

ላገኛት ስላልቻልኩ ባገር ውስጥ እናቴ
ልፈልጋት መጣሁ ሳሰሁ በህይወቴ
ስመድረስ ሰኳትን ካሰችበት አገር
እናቴን አያሰምኩ ቀን ተሌሊት ስጥር

በድንገት አገኘሁ ያልጠበቅኩት ነገር
እናቴን ስፈልግ ሌላ እናት አገኘሁ!
እሰከዛሬ ድረስ እዚያው እናራለሁ
ለካስ ይሄም አለ ሁለተኛ እናት
በፀባይ ከያዟት ትበልጣለች ከእናት
እናቴ አታኩርፊ ፍለጋ አላቋርጥም
ፍጹም አልዘናጋም ተስፋዬን አልቆርጥም
መንገድ ያገኘሁትን ፋንታሽን አመጣለሁ ለብቻዬ
አልበላም
ክረምቱ አባርቶ አትላንቲክ ሲስከን
እንገናኛለን እግዜር ሲፈቅድልን
እንደተለመደው እጅሽን ዘርግተሽ ፀሎት ስታደርሺ
የኛም የልጆችሽን አቤቱታ አትርሺ

አገሬ ቆንጆ ናት

አገሬ ቆንጆ ናት ህዝባችን ደግ ነው
እንግዳ ይወዳል ያበላል ያጠጣል
የሰው እግር ያጥባል አልጋውን ይለቃል
መቀበል መሸኘት ማሰተናገድ ያውቃል
በበጎ ለመጣ ያሰውን ይቸራል
በከፉ የመጣ አባሮ ይቀጣል
ጫማ አስወልቆ አጽድቶ ይስጣል

ትዳር እሹሩሩ

የባልና ሚስትን ችግር! የሚያነሳ
በትዳር መካከል! አያሻም ደላላ
ነገር አውጋሪጋሪ ጠንቅ የሚሆነውን
ገንዘብና ሀብት ምስጢር አባካኙን
ፍቅርና ምስጢር ቤተሰብ በታኙን።

አለማሰገባት ነው፤ሶስተኛ ወገን
ግዙፉን ጉልጅ ቤት ንብረት ሥንሰራ
ሕይወት ለንፈጥር ልጆች ስናፈራ
እርስ በርስ ስንመካከር ያን ሁሉ ስንተባበር
ብዙ ዘመን ኖረን በፍቅር ስንግባባ በሀሳብ ስንለያይ
መቼ አሰፈለገን የነገር ገላጋይ
ባለፍናቸው ጉዞ ያካበትነው ሀብት ያሳደግነው ትዳር
መልሰን በማፍረስ ለፖሊስ ጠበቃ ለዳኛ መገበር
ለመሬ ሱሰኞች ስኒ መጨበጫ
ለቢራ ፈላስፎች ለክሮ ማላገጫ
አማካሪ መስለው ውር ውር የሚሉት
ለግንም ባል አይሆኑም ለግንም አይሆኑም ሚስት
የተጋባንበት ቃል ኪዳንን አጥፈን
ባደባባይ ቆመን ምስጢር እናባክን
ትዳር ካሞከቡት ትዳር ካሞረዱት
ንቀው ችላ ካሉት፣ካልተንከባከቡት
እንደ ልጅ ያኮርፋል
ይራባል ይጠማል ጠውልጎ ይደርቃል
ከልብ ከጠበቁት ከተንከባከቡት
እሹሩሩ ካሉት
አብቦ ያፈራል እድሜ ልክ ይዘልቃል
ለልጅ ልጅ ይተርፋል
ትዳር ከቡር ነገር ነው ሁሉ እንዘልይለት
ሱባኤ እንግባለት መዝሙር እንዘምርለት
ባይዘፍን እንዝፈንለት ባያስቅ እንሳቅለት
ከራር እንደርድርለት ከበሮ እንምታለት
መለከት ይነፋለት
እንከባበው እሹሩሩ እንበለው
ትዳር ይህ ነው የሚወደው

<u>ለደተኞች ድሆች</u>
ወራቶች አለፉ ዘመናት ከነጉ
በጨቅላ ሥራችን ለቀው እያሾፉ
ትተውን ተጓዙ ለው ፍለጋ ሄዱ
በኛ አለመንቃት አየተናደዱ
የጎላ ማሕበር የጎላ ውድድር
ንትርክ ጭቅጭቅ ምን ይጠቅማል ለአገር
አጉል መመጻደቅ ካልሆነ መጸጸል
በዘር በሓይማኖት ማን ከማን ይበልጣል?
በእምላክ ሥራ ንብተን በከንቱ አየዳከርን
የፍቅር የሥራ ጊዜአችን አባክን
ወደኋላ ሄድን
ውድ ዋጋ እየከፈልን ይኸው አዚህ ደረስን
የዓለም መጀመሪያ የድንቅነሽ ልጆች
ያልተባልነው የለም ያልተሰጡን ስሞች
ረሀብተኞች፣ድሆች፣ ኋላ ቀሮች፣... ለደተኞች

<u>የዚህ ዓለም ኑሮ</u>
ለው ከቡር መሆኑን አልታይ አያለን
በጅ ያለውን አይተን ቶሎ አንፈርዳለን
ሚዙን አንዳይዛባ አድልዎ አንዳይኖር
ነገ በኔ በማለት ፍርድ ከራስ ብንጀምር
ለፍትህ ብንቆም ለዕውነት ብንጥር
አንድ አንዱን ባይጨቁን የለው መብት ቢከበር
የዚህ ዓለም ኑሮ ገነት ይሆን ነበር

***አመዛዝኖ መርገጥ**

የሰው ልጅ ለመኖር
ከችግር ለማምለጥ ይድሃል ይርጣል
ዳገት ቁልቁለቱን ይወጣል ይወርዳል
የፈለገው ሲያጣ ያዝናል ያማርራል
ሞራሉ ዝቅ ይላል ከሰው ይደበቃል
ደስታ ሲገጥመው ብዙ ይፈነድቃል
ሃብት ንብረት ሲቋጥር በኩራት ይዋጣል
በጣም አለመቅበጥ ብዙም ላለመተከዝ
ሚዛኑ ጠብቆ ነው አመዛዝኖ መጓዝ
ውጣ ውረድ በዝቶ ከላይ ከመፈጥፈጥ
እያዩ መጓዝ ነው አመዛዝኖ መርገጥ

ሥልጣኔና ሰው

የሰው ልጅ ሰልጥኖ እጅግ ገሠገሠ
ከምድር ተወንጭፎ ጨረቃ ደረሰ
አይኑ ሲገለጥ እንደ አዳምና ሔዋን እየተመራመረ
የእግዜር ሥልጣን ተጋፍቶ ራሱንም እንደ ሸክላ
መጠፍጠፍ ጀመረ
ሰውና እንሰላ ሁሉንም በአምላኩ
ሁሉም አይነት ፍጥረት ሠርቶ አሰመርቋል አሉ
ምን ይሽ ብቻ የሰው አካለ ዘር ሸንሽኖ ቆራርጦ
ሀይማኖትን ሽሮ የእግዚአብሄር ሕግ ሰውጦ
ሰርቷል ሴትን ወንድ ወንድን ሴት አድርጎ ዖታ ገለባብጦ
አወይ ሥልጣኔ! በውሰጡ ስንት ጉድ አለው
የሴትም ወንድ አላት የወንድም ሴት አለው

የሰው ልጅ ይረሳል

ማንም የማይገታው
የተፈጥሮ ሕግ ነው
ጊዜ ይቀያየራል ወቅት ይፈራረቃል
ሀብታም ይደኸያል ድህ ይበለጽጋል
ሕጻን ይወለዳል አርጅቶ ይሞታል
ፀሀይ ትጠልቅና ጨለማ ይሆናል
የተራ ጉዳይ ነው አንዱ ሌላ ይተካል
ይህ እንደሚሆን ግን የሰው ልጅ ይረሳል

ምን ልናወርስ ነው

የበለጸጉ አገሮች በሃብት የመጠቁት
ሕዋውን ሸንቁረው ጠፈር የደረሱት
ዘዴና ብልሀቱን ከወዴት አመጡት
እኛስ ኢትዮጵያውያን እንዴት እናድጋለን እንሻሻላለን
ሰው ከደረሰበት እንዴት እንደርሳለን
ከሰዎች ካልተማርን በራሳችን ካልጣርን
በሕብረት ካልተጓዝን ጠንክረን ካልሠራን
ካልተደማመጥን ፍፁም ካልተቻቻልን
ካልተቀራረብን፡ አገርና ወገን በጋራ ካልጠበቅን
አንዱ አንዱን ሲበድል፡ ተው አታድርግ ካላልን
ሌላውን ሲያጠቃ መሳሪያ ከሆንን መሳሪያ ካቀበልን
ለጋራ ጥቅማችን መመካከር ካልቻልን
በሄድንበት ሁሉ በመሸበት ካደርን
እንዴት እናድጋለን እንበለጽጋለን?
ሰው ከደረሰበት እንዴት እንደርሳለን
የወረሰናቸውን ተንከባክበን ካልያዝን
የተፈጥሮ ሀብታችን ካልተንከባከብን
አንድ ዛፍ ሳንተክል ብዙ ከቆረጥን

ደን ካቀጣጠልን አከስለን ከሸጥን
ሀውልቶቻችን ሲፈርሱ፡ዝም ብለን ካየን
ውርስና ቅርሳችን አየሰረቅን ከሸጥን
ካልተደግመጥን በሆነ ባልሆነ ከተጨቃጨቅን
በከብ ጠረጴዛ መነጋገር ካልቻልን
የወረስናቸውን ለተተኪው ትውልድ በከብር ካላስረከብን
ምንድነው ነው ራዕያችን
ወዴት ነው ግባችን
ምን ይዞ ጉዞ ነው ለልጅ ልጆቻችን

<u>ሰኳር የበዛበት</u>
ቆፈንና ንዳድ ተራ የገቡበት
ሀብትና ድህነት ሁለቱም ያሉበት
ሱረትና አብደት ሚዛን የደፉበት
አርቲፊሻል ምግብ አሻንጉሊት ነገር
በብዛት ያሉበት
በቀንም በሌሊት የሚመረትበት
የጂት ሞተር ጉጥም ሰው የሚከነፍበት
በጣፋጩ ብዛት ሰው የጣፈጠበት
ደም፣ስጋ፣ አጥንቱ፣ስኳር የሆኑበት

<u>በግስረጃ ይሁን</u>
.ከሰለጠነው ዓለም ትምሕርት አንቅሰም
.በወሬ መጠመድ መጠፋፋት ይቁም
.ነገር ወዲህ ወዲያ አሉባልታ ይብቃን
በውሸት ፈጠራ ሰው መወንጀል ይቅርብን፣
.ከሰና ክርክር በግስረጃ ይሁን።

<u>የነቃ ሕዝብ</u>
አንድ ጥይት ሳይተኮስ
አንድ ጠብታ ደም ሳይፈስ
አንዲት ቅጠልም ሳትበጠስ
የህዝብ ሰላም ሳይደፈርስ
የልማትም አውታር ሳይፈርስ
ይቻላል የዲሞክራሲ ሥርአት ማንገስ።
በበሳማዊ ትግል ፍትህና እኩልነት ማንገስ
ሕዝብ አንድነቱን ካጠናከረ
ሳፋይከፋፈል ከተባበረ
በጋራ ጥቅሞቹ ላይ በሕብረት ከመከረ
በጋራ ችግሮቹ ላይ ካተኮረና ከመከረ
አንድ ቃል አንድ ቋንቋ ከተናገረ
ይችላል ህዝብ የመረጠውን ሊያራምድ ያልፈለገውን
ሊያስወግድ
የነቃ የተደራጀ ሕዝብ ትግል
ፍቱን መድሐኒት ነው ሁሌ ያሸንፋል።

<u>አባይ ባንደበቱ</u>
ኢትዮጵያና ኡጋንዳ ሁለቱ እግሮቹ
ከሱዳን ላይ ስደርስ ያጋቱ ጡቶቹ
ግብጽ ላይ ስደርስ ያለቅላሉ አይኖቹ
ካገሬ ወጥቼ ስንከራተት ውዱ ባዝኜ ባዝቼ
ልጆቼን ተጠምተው አገሬን ከድቼ
ሕይወቱ ያከትግል ቀይ ባሕር ጉበቼ

እኔም ተሰድጂ ልጆቼም ተሰደው
ተበታትነን ቀረን ተዛበተብን ለው
ሰምች ቢታዘቡን ቢንቁን ቢጠሉን
ድሆች ሰደተሞች... እያሉ ለደቡን
እኔም ተሰድጂ ልጆቼም ተሰደው
ተበታትነን ቀረን ተዛበተብን ለው
ወይ ጡቴን አልጠቡ ረሐብ ሲፈጃቸው
ወይ ቀድተው አልጠጡኝ ውሀ ሲጠማቸው
ባገሬ እንድኖር ምንም ላይደክሙልኝ
ሰማሁ ሲያግርሩኝ እጥብቀው ሲወቅሱኝ
አባይ ግደሪያ የለው ግንድ ይዞ ይዞራል ብለው
ሲዘፍኑብኝ
እባይ ቢሞላ አለው መላ መላ ብለው ቀለዱብኝ
ልጆቼም ርቀው ሄዱ ቀሩ በሄዱበት
ከርመው ውለው አደሩ ለወጡ ዜግነት
እኔስ ብዙ አልራቅሁም ራሴ በኢትዮጵያ እግሬ ከቀይ
ባሕር
ሆድ እንጀቴን በላው የልጆቼን ነገር።
የግዮን እምላክ ትዕዛዝ መቼ ተከበረ
የተለጠኝ ሥራ ኢትዮጵያን ማጠጣት ማለምለም ነበረ።
መወቃቀስ ይቅር ያለፈው ይበቃል
ተበታትኖ መኖር ለዚህ አብቅቶናል
ምክሬን ተቀበሉኝ ኑዛዜዬን ለሙኝ
እባካችህ አልሙኝ እባካችሁ ጡሩኝ
እኔም የናትነት ወግ ማዕረግ ይድረሰኝ

ቡልኮ አልብሱኝ ጋቢ ደርቡልን
በሕልፈተ ሞቴ ባገሬ ቅበሩን

**<u>በአሜሪካን አገር</u>
አየር ለመቀበል ወጥቼ ከሰፈር
በጉዴ ወጣሁኝ አሜሪካን አገር
ካለሁበት ሰፈር ቅያሱ እሳሰቶኝ
እድራሻዬን ሰቼ ሌላ ቤት ደረስኩኝ
ከተከፈተ ቤት ዘው ብዬ ገባሁኝ
በሶፋው እቀማመጥ በዕቃው ትርምስ
ግራ ቀኝ ማትሬ ፍጹም ግራ ገባኝ
ቤቱ አለመሆኑን ሁኔታው አስረዳኝ
ጨንቆኝ ድንግር ብሎኝ ዙሪያዬን ሰማትር
ሁለት ሰዎች ወጡ እያሉ እንቸር እንቸር
እበሻ የሚመስሉ ጠይም ሰዎች ናቸው
እንደተደናገጥኩን ባንድ ጊዜ ገብቷቸው
ኢትሰ እኬ አሉኝ እኔም ታንክዩ እልኳቸው
ወሬውም ቀጠለ በተቻለኝ አቅም ነገር በምልክት
በመሃይም ዜዴ ማስረዳት ጀመርኩኝ
ነገሩ ገባቸው በጅጉ ተግባቡኝ
ለዎቼ ደግ ናቸው የሚበላ መጣ ኧረ ስንቱ ቅጡ
እትክልት ፍራፍሬ እንዲሁም መጠጡ
ሁሉም ቀረበና በልቼ ጠጥቼ
ሶፋው ላይ ተጋደምኩ ትጥቄን እላልቼ
እጅግ ተመችቶኝ እንቅልፍ ሲከጅለኝ

ሰምን እንደሁ እንጃ አንዱ ሰው ተጠጋኝ
ወንድ ነህ ሴት አሰና ጠየቅኝ
ያልተላጨ ጢሜን ሁሰንተናዬን እያየኝ
በምን ጠርጥሮኝ ነውና እንዲህ የጠየቀኝ
እኔ አበሻ ወንድ ነገር ከከጀሰኝ
አሳየዋለሁኝ አልኩና ወሰንኩኝ
ወዲያው ሰውነቴ አናቴ ነዘረኝ
የሞት ሞቴ ስሞት ወለል ብሎ ታየኝ
ዱላዬን ሙሾርጨ ዘራፍ ዘራፍ እያልኩኝ
በጣም ተቆጥቼ ተስፈንጥሬ ቆምኩኝ
እኔ ከሶፋው ላይ እነሱ እዚያ ግዶ
ተፋጠጥን ሬት ሰፌት ወይ ነዶ ወይ ነዶ
አተኩረው ሲያዩኝ ብትር እንሰቻለሁ
ሥሬ ተገታትሮ ግሥላ ሆኛለሁ
ዱላዬን እንስቼ ከፍ ከፍ አደረግሁት
በነሱ አቅጣጫ እጀን ሰነዘርኩት
አየሩን ቆረጥኩት በቁም ሰነተቅሁት
ጮኽና ተሰማ አለ ሸ፡ተ፡ተ፡ት
በማክታተልም ለመምታት ሰንዝሬ
ሀሳቤን ሰውጪ ተወንጭፈ ወጣሁ በመስኮት ተወርውሬ
ከብሬን ሳላስነካ መብቴን ሳላስደፍር
ያላላሁትን ሳላጠብቅ የፈታሁትን ሳላስር
በመስኮት ዘልዬ አመሰጥኩኝ ባጥር
እግዜር ትረፍ ሲለኝ ውቃቤዬም ነግሮኝ

ዱላ ይዤ ነበር ውሻ እንዳይነክሰኝ
ምርኩዝ እንዲሆነኝ
በዚህ አይነት ወኔ እኔና ብትሬ ጠላት
አስፈራርተን
ብሎም ድል አድርገን
ባገሬ ቀረርቶ ሽረ ጎራው ብለን
ሽልለን ፎክረን፡ ትዕይንት ታሪክ ሰርተን
በማናውቀው አገር በድል ተመለስን፤
ከችግር እምልጠን ከቤታችን ገባን
እግዚአብሔር ይመስገን
<u>ብትር</u>
አሜሪን አገር የተወለዳችሁ
ከኢትዮጵያ መጥታችሁ ዱላ የረሳችሁ
ብትር ታውቃላችሁ ?
ሰጊዜው ሲያዩት ገራገር ይመለሳል
አበሻ ብልጥ ነው ይመረከዘዋል
ያገሬ መሳሪያ ዱላ ቅዝምዝሙ
ላወቀበትማ ሰተረዳው ጥቅሙ
ክፉ ቀን ሲያጋጥም ጥቅም ላይ ይውላል
ጠመንጃ ያስጥላል ሽኮና ይጠልፋል።
እንገት ቅንጥስ አርጎ ቆራርጦ ይጥላል።
በጨለማ ጊዜ አቀበት ቁልቁለት
ምርኩዝ ይደረጋል
ቅዝምዝም ሰንዝሮ ከወረወሩትም
ኢላማውን ይመታል በፍጹም አይስትም

ከራሰ ላይ ካረፈ አያድርሰ ነው ከቶ
ጨፍጭፎ ይገድላል ፈንክቶ ፈንክቶ
ጥይት አያሻውም ፈቃድ አያሻውም
በቀላል ይገኛል ርካሽ ነው ዋጋውም
በወንጀለኛነት አይጠረጠርም
በፍተሻ ያልፋል ፖሊስ አይዘውም
የትም ቦታ ይሄዳል ይገባል ይወጣል አይከለከልም
ከኋይት ሃውስ ቢሆን ቤተመንግስት የትም ይሁን የትም

<u>ቀጠሮ ይከበር</u>
ሰላምታ አየለጠ ደህና ሁኑ አያሰ
አርጌው አሰፈ አዲሱ ከች አለ
በዓላቶች መጡ ተመልሰው ሄዱ
ሮጡ ገሰገሱ አለፉ ነጎዱ
ሠዓቱ ይቆጥራል ይፈጥናል ይከንፋል
ጊዜ እያለፈ መሆኑን ያሳያል (ይነግራል)
ሴኮንዲም በፍጥነት ትሽከረከራለች
ቀይ ቆብ አድርጋ ታስጠነቅቃለች
ደቂቃም እንዲሁ ወደፊት ይጓዛል
በአምሰት በአምሰት ከፍሎ መድቦ ያሳያል
ሁሉም ይጓዛሉ ይሽከረከራሉ
ጊዜ ይሄዳል እንጂ አይቆምም አያሉ
አንደኛው ሲፈጥን ሌላኛው ቢያዘግምም
መቆም ወይ መቀመጥ ጨርሰው አያውቁም
ትሽከረከራለች ከቢቷ መሬት

ይፈራረቃሉ ቀንና ሌሊት
ብልሁ ይጥራል ይሰፋል ያመርታል
ሰነፉም እንዲሁ በቁም ያንቀላፋል
አዳዲስ ግኝቶች በዓለም ላይ ሲሰፉ
ሰዎች ከንፍ አብቅለው ሰማየ ሰማያት ሸንቁረው ሲያልፉ
ብዙ ሰው ተኝቷል አልነቃም ከአንቅልፉ
ውድ ሰዓት ከመዛት በጌጥ ከማሸቀርቀር
ጊዜ ይበልጥ ዋጋ አለው ቀጠሮ ይከበር

<u>የክራዲት ምስጢር</u>
መኖር መታገል ነው መታገልም መኖር
ሲዋትቱ ውሎ ሲባንኑ ማደር
ጣምራ ጦርነት ነው የዚህ ምድር ምስጢር
የሰዉ አጨካከን የዕዳው ጋጋታ
የቴሌ ማርኬቲንግ የሚጎርፈረው ፖስታ
ይህ ሁሉ ሽርጉድ የውሸት ሰላምታ
ማባበያው ሺህ ነው
ብድር እንዲጠየቅ ነው ወይ እንዲገዛቸው
ወትውተው ደልለው አባብሰው ጀንጅነው
ሁሉም ነጻ ብሰው ሁሉም ዜሮ አድርገው
ከፊት ጣፋጭ ነገር ከኋላ ተብትበው
በጥቃቅን ጽሁፍ ምስጢሩን ደብቀው
ባካፋ ለመውሰድ በማንኪያ ለመስጠት
ማባበያ ለማላስ ወጥመድ መረብ ጥሰው
ያቺ የሰው ታርጋ ሶሻል ሴኪዩሪቲ

አሳባቂ መልቲ
አንዴ በጅ ካስገቡ ጽፈው ከከተቡ
በስንክ ሳር መዝገብ ጭረው ከዘገቡ
ከያዘ የማይለቅ መንጠቆ ከሳቡ
ገመዱን ወርውረው ባንገት ካጠለቁ
ሽምቀቀው ካነቁ
ሞተ አከተመ አያነቃንቁ
ቆሞ መታሰብ ነው የዋጡትን መትፋት
ጨንራ ገልብጦ የገባውን ማውጣት
ክሬሙን ሲዝቁ ሲያወጡ ሲያወጡ
ከፈሰጉት ብልት አማርጠው ሲቆርጡ
እስከ መጨረሻው እስከ አንዷ ደም ጠብታ
አጥፍፎ መስጠት ነው ቆሞ በጸጥታ
ሌላ የሚገርመው የሰውን ማንነት ደረጃ ለመስጠት
መሆኑ ይገርማል መስኪያ ሚዛኑ በዕዳዎቹ ብዛት
አንዲያ እንዲሆን ነው የተቆላለፈው
በዚህ አንዲሆን ነው ሥርአቱ የቆመው።
ምን አይነት መንገድ ነው የክሬዲት መንገድ
አሰፈርሞ ሠጥቶ በሰውር የሚወስድ
ሰውነት ላይነካ በስለት የሚቆርጥ
ባየር ተወንጭፎ የሰው ደም የሚመጥ
ከምስጢር ኪስ ገብቶ ዶላር የሚያሟጥጥ
ሠርቶ የደበቁት ከባንክ ውስጥ ሳያድር
ገንዘብ የሚቀማ በረቀቀ ዘዴ በውስብስብ ምሥጢር
ቋንቋ ላይ ተቋጥሮ አፍችን ለጉሞ

በውስብስብ ሂደት ያለአንዳች ተቃውሞ
አፍንጫ ስንነ የሚያልብ አስቁሞ
ወጪው ግን ይሆን ዋጋሞቱን የሰራው
ሳይንቲስት ፈላስፋው የመጀመሪያው ሰው

<u>የአንድ ሰሞን ሕብረት</u>
የአንድ ሰሞን ሕብረት የውሸት ቲያትር
ስለሚያደናግር አያሻንም ይቅር
ጊዜያዊ ሕብረት
ሊባል ይገባዋል ላጠራና ወንፊት
እኛ የሚያስፈልገን ዕውነተኛ ውሕደት
የስመረ አንድነት

<u>ግሊያንና እንግሊዝ</u>
ደንደስ ጡንቻ ያላቸው
ግሊያንና እንግሊዝ ትልቅ ምሽግ ስርተው
እንደፋሮ አውሬ መሬት ጉድጓድ ምሰው
በሊሬ በፓውንድ ብዙ አሽከር ገዝተው
ወገን አሸፍተው ዜጋ አስኮብልሰው
ሆዳም አስባስበው ባንዳ አሰልፈው
ምላሰኛ ቀጥረው ቀጣፊ አዝምተው
ወረውን ነበረ ገዝተውን ለመኖር
በሕብረት ለመበዝበዝ ተዘጋጅተው ነበር
የኢትዮጵያ አምላክ የሰሩት ግፍ አይቶ
ለጀግኖቻችን ጉልበት ብልሀት ሰጥቶ

በመጠብት መንገድ ሳይውሉ ሳያድሩ
ብዙ ዋጋ ከፍለው ተዋርደው ተባረሩ
በሰፈሩት ቁና ወዲያው ተሰፈሩ

<u>ሥርዓት ሲያረጅ</u>

ሥርአት ሲያረጅ
እድሜው አብቅቶ ሲሻጅ
መቆም አቅቶት ሲንገዳገድ
ጊዜው አከትሞ ሲዋረድ
ሽባ ሆኖ ሲሽመደመድ
መላቅጡ ቅጡ ጠፍቶት ሲወላገድ
ከሞት አፋፍ ሲደርስ
አይቻልም ወደቀድሞው መመለስ
ቀለም ቀብቶ ማደስ
ቢገድቡት አይቆምም
ቢሰምኑ ቢግጹ አይመለስም
ጣጣ ፈንጣጣው ይበዛል
አልጋው ፍራሹ ዘውድ ዙፋኑ ይናጋል
ይንቀጠቀጣል ይንዘፈዘፋል ይፍረከረካል
መሠረቱ ተሰነጣጥቆ ይፈራርሳል
ስለሆነም አይቻልም ወደ ነበረበት መመለስ
ጠግኖ ደርቶ ማደስ
የሕይወት ጊዜው ያበቃል
የሥርአት ሹም ሽረት ይከሰታል
በአርጌው መቃብር አዲስ ተረግዞ ይወለዳል

መሪዎች ገና ከወንበር ላይ ሲወጡ
ሥልጣን አግኝተው ሲቆናጠጡ
ልባቸው መጠኑን አልፎ ያብጣል
ሞት መኖሩንና ሰው መሆናቸውን ይረሱታል
ተዕቢትና ትምክህት በውስጣቸው ይነግሳል
ሐይማኖታቸው ይጥፋል፡ ቃልኪዳናቸው ይፈርሳል
እኛቸው በወንጀል ይጨቀያል ይረክሳል
ሥርአታቸው ሲያረጅ
ዕድሜው አብቅቶ ሲሻጅ
ነጋሪት ቢያስሙቱ ቢያለቅሱ ቢፀፀቱ
ሆኖ ይቀራል የከንቱ ከንቱ
አንዲያ አንዳልነበረ ምኞታቸው
አንዲያ አንዳልተፈራ ሥርአታቸው
ይበረክታል ውርደታቸው ይፋጠናል ሞታቸው
ቢያስልፉ የሰራዊታቸው ብዛት
ቢጠቀሙ የባሕር የአየር የምድር ሀይላቸው ብዛት
አይቻላቸውም ሥርአታቸው እንደነበረ ሊያቆዩት
የሰው ልጅ ከዚህ ምን ይማራል
መልካም ስርቶ ማሰፍ ከሁሉ ይልቃል
በሰማይና በምድር ያስመሰግናል።

<u>ከአቅም በላይ መኖር</u>

አደብ ግዛ ልብ ሆይ ተረጋጋ ዝግ በል
ልብ ግዛ ልብ ሆይ ቀስ በል ሰክን በል
ተመከር ልቦና አትሩጥ አትቅበጥ

እንደ ሮሌ ፈረስ ደንገላሳ አትርገጥ
በሰው አገር ባሕል ባለመድከው ፈሊጥ
ገብተህ እንዳትሰምጥ መውጫ አጥተህ እንዳትቀልጥ
ሰከን አደብ ግዛ አርጋ ተረጋጋ
አይቶ ያልረገጠ ይወድቃል ከአደጋ
ልብ ግዛ ልብ ሆይ ተለመን ቀስ በል
በደመነፍስ አትኑር ግራ ቀኝ አስተውል
አርቆ ለሚያይ መንገዱ ቀና ነው
ተግተህ ተመራመር አጣጥመህ እየው
ከአትም በላይ ሱስ እንዳይለከፍህ መርምር
ከወጪህ ተቆጠብ ከሥራ ግን ጠንክር
አንገትም አባክህ አዙረህ ተመልከት
አንቅፋት መሰናክል እንዳይገጥምህ ድንገት
አይንም ከፉና ደግ አጥርተህ አይበት
የጎረቤት አይተህ ሰታልም አትደር
የቆምክበት ሥፍራ ሰማጤን ተጣጣር
አግርም አይተህ ተጓዝ አቀበት ቁልቁለት
የብልህ አርምጃ ጥንቃቄ አለበት
ኪሰም ቀዳዳውን በፍተህ ተቆጣጠር
ሮሌ እንዳይዘርፍህ ተጠንቅቀህ ጎበር
የልብ ጓደኛ አንጎል አድብ ግዛ
ግዴታህ ተወጣ አጉል አትንዛዛ
የሰው ኑሮ ቀስመህ ስትጣንን አትደር
መደመር መቀነስ ማባዛቱን ተማር
በፍጹም አትኮርጅ የሌላን በማየት

አካሎች በሕብረት አንድ ላይ ምከሩ
ለአንድ ወጡ አካል ጠንክራችሁ ሥሩ
በህብረት የሠራ ከግቡ ይደርሳል
ድልን ይቀዳጃል ጠላት ያሳፍራል
ተባብሮ በመሰራት ድንቅ ሥራ ሥሩ

<u>አሰን አንዳንድ ሰዎች</u>

ከንፍ አውጥተን በራሪዎች
ብድር የማንፈራ ብኩኖች
የተበዳሪ ተበዳሪዎች
ለመጣጣር ደካሚዮች
የሳንቲም የቤሳ አሳዳጆች ተገፊዮች
እንደመሩን የምንፈሰ የቦይ ውሀዎች
በሰው አሳብ ተመሪዎች1 በሰው ትእዛዝ ተንቀሳቃሾች
ከመሮጥ በስተቀር አማራጭ የማናውቅ ሰዎች
የዝይ ከንፍ አብቃዮች
የኛን አጣጥለን የሰውን አድማቂዮች
የራሳችን ሲያር የሰውን አሳማዮች
ለገዛ ጥቅማችን ድምጽ የማንሰጥ ጉዶች
የማንደማመጥ የማንስማማ ሰዎች
የሚነቀፈውን የምንደግፍ1የሚጎዳንን የምንደግፍ ቡድኖች
የጎረቤት ምግብ የለው የሚጥመን
የራሳችን ጉዳይ ደንታ የማይሰጠን
ትንፋሽ ተሰፍሮልን1 ደስ ብሎን የምናድር
የትም የምንለምድ1 አለን ብዙ ፍጡር

እንገት አቀርቅረን፤ዝም ብለን የምንኖር
ሁሉንም ቅርጽ የምንይዝ ባለብዙ ፈርጆች
ቀለም መለዋወጥ የምናውቅ፤በመልክ ለው መለዮች
በተግባር አፈንጋጭ፡ የኛ ብቻ ባዮች
በመሸበት የምናድር አለን አንዳንድ ለምች
ያደርንበት ዛፍ የምንመለል ጉዶች

<u>ገመድ ጉተታ ላይ ነን</u>

እድሜ መስተዋት ነው ሁሉም በታ ደረሰን
ያልሰማንውን ለማን ያላየነውን አየን
አገራችንን ቆርሰን ዳር ድንበር አስፈረስን
በዘር ተከፋፍለን የጎሪጥ ተያየን
አማራ ጉራጌ አሮሞ ተባብለን
ዘር ዝርዘራ ገባን ዘር ቆጠራ መረጥን
በስጋ ተጣላን አጥንት ተቆጣጠርን
ቀፍቅፈን ፈልፍለን መከፋፈል ሰርተን
የኛ አሰፖርት እሱ ነው ገመድ ጉተታ ላይ ነን
አለፉ ዘመናት እንደዚያ እየሆንን

<u>ለከሃዲና ጨካኙ ጓደኛዬ (በነጠላም በብዙ)</u>

ምስጢር ላልመረምር
ምንም ላልጠረጥር
ያባትና እናቱን የዘር ግንዱን ለይቼ
የአገሬ ልጅ ነው ብዬ ሀይማኖቱን አይቼ..
ይሉኝታ ያከብራል ይመዝናል ብዬ
ከአሳር አንዲያወጣኝ ባቀብለው እጄን

ብከፍትለት ልቤን
የጉድ ጉድ አረገኝ
እደራዬን በላኝ እምነት አጎደለብኝ
በከሀዲት ላይ ከሀዲት ሽምጥጥ አርጎ ክዶ
ከመርከብ አውርዶ
ተስፋ ከሌለበት ከባህር ላይ ጣለኝ
የሱ አይነት ከሀዲ
መጠርጠር፤መመርመር፤ማወቅ፤ነበረብኝ
ለአደራ የማይበቃ አሞራ መሆኑን
ቂም በቀል ማርገዙን ተንኮል መሸመቁን
አትርፎ ሊሸጠኝ ቃል ኪዳን መግባቱን
ለጥቅም መቆሙን ፈርሞ መምጣቱን
እዚህ ላይ ይበቃል ታሪኩ ተዘግቷል
ፈጣሪ ፈርዶታል ዋጋውን ከፍሎታል
ሲወዱት ለጠላ ሲያምኑት ለከዳ ለው
ከጂው <u>መሬት</u> ከድቶት ብድሩን አገኘው

<u>የኢትዮጵያ ምድር</u>

ኢትዮጵያ የሚሏት ጥንታዊቷ ምድር
ተጽፋ ያለችው በፈጣሪ ብዕር
ሉሲ እናታችን ድንበራችን ታርዳን
ትምጣና ትናገር
ከምስራቅ ኢትዮጵያ ከአውሳ አፋር ምድር
ከለሜን ኤርትራ እስከ ኬንያ ድንበር
ከሱዳን ኑብያ እስከ ቀይ ባሕር በር
ተፈጥሮ ድንቅ ነው እንደለው አይዋሽም
ሥልጣን ወይ መታያ ጥቅም አይፈልግም
ከቆመበት ሥፍራ አይነቃነቅም

ጠላትን አይፈራም ከቦታው አይሸሽም
የአፄዎቹ ግንቦች የአሪት ሃውልቶች
ምልክቶች ናቸው የጥንት ምልክቶች
ስለ አገር ዳር ድንበር
አስብ ምጽዋ ዳህላክ ቀይባሕር
የቀድሞ ወደባችን አዱሊስ ይመስከር
ዛሬ የማን ናቸው ጥንት የነማን ነበር
ኢትዮጵያ ሰሚ ውይ
ጥንግ ድርብ ጥበቧ
ወንዞች መቀነቷ
ወርቅ ማእድን ውበቷ
ተራራ ሸንተረር ቆንጆ ደም ግባቷ
በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብዙ ጊዜ የተጠቀሰችው
በዓለም ቅርስነት የተዘከርችው
ጥንት እንዲህ ነበረች በኛ ዘመን ከሳች
ዘመን ተቀይሮ ከዚህ ላይ ደረሰች
የድሮና የአሁኑ ሂሳቡ እንዳይምታታ
አንባቢ ይገምግም ያስችበት ቦታ

<u>ማነው ኢትዮጵያዊው</u>

አንዱ ከሌላው ዜጋነ በተግባሩ ይሰይ
አረንጓዴ ቢጫ ሕብረ ቀለማም ቀይ
ዛሬ ኢትዮጵያዊው ማነው?
ምስልና ቅርፁ አባቱ የሚመስለው
በመከራ ጊዜ አናቱን ያልራቀው

ለወንድም እህቶቹ መከታ የሆነው
ጥሪ ሲቀርብለት ምላሽ የሚሰጠው
ስንፈት የሌለበት ያልተበከለ ሰው
የአያት ቅድመ አያቱ ምክር የወረሰው
በእንዲታ ኢትዮጵያ በራሱ እምነት ያለው
የአገሪቷን ታሪክ አውቆ የተከተለ
በዘር ወረት ሰምጦ እጁን ያልበከለ
የአገር የባንዲራ መዝሙር የሚቀበል
እኔ አበሻ ነኝ ኢትዮጵያዊ የሚል
አገር ወዳድ ዜጋ ወረት ያልበከለው
እናቱን ያልዋሸ ጥቅም ያለወጠው
በኢትዮጵያዊነቱ በሕግ በኑዛዜ ሰውርስ የሚበቃው

<u>ዓለም</u>

ሰዎች ሥርዓት ጥሰው ግብ ግብ ሲገጥሙ
ሕግጋትን አፍርሰው ጥፋት ሲፈጽሙ
ዓለም በሰው ሥራ ስትናደድ ስትተክን
መልካም ነገር ጠፍቶ ሲበዛባት ሃዘን
ሰዎች እየቀበጡ ቫይረስ ሲለቁባት
መድሀኒት የሌለው ደዌ ሲያሰፍሩባት
ኤቦላ፤ኤድስ፤ናይል ቫይረስ ሲነሰንሱባት
በኑክለር በሚሳይል በቦምብ ሲያነዷት
ከዓለም ሲጠፉ እግዚአብሄርን መፍራት
በሰው ልጅ መካከል ጭካኔ ሲበዛ
መባሪያ ሲሠበቅ ጦርነት ሲታወጅ በዋዛ ፈዛዛ

ሰው እርሙን ሲበላ ተንኮል በዓለም ሲነግሥ
ምድር በሮኬት በታንክ ስትታረስ
ንዴትዋን ሰመግለጽ፤ በጣም ትቆጣለች
በምትችለው ቋንቋ ሃሳቧን ትገልጻለች
ትንቀጠቀጣለች ትንዘፈዘፋለች
በነፋስ በማዕበል ቀውጢ ትሆናለች
አንዴ ትሞቃለች አንዴ ትወጅባለች
በጎርፍ በውሽንፍር ትጥለቀለቃለች
መፈንዳት ትሻለች መናጥ ታበዛለች
ክፉ ሥራ እንዲቆም ታስጠነቅቃለች
የእግዜር ቃል እንዲሰማ በለሆጅ ትነግራለች
ሰው ግን አይግርም
ከግጥፋት አይቆምም

<u>የተሥፋ ምድራችን (ራዕይ)</u>
ፍልስጥኤም ለፍልሰጤማውያን
ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን
አበሲኒያ የተፋ ምድራችን
ታሪካዊቷና ብርቅየ አገራችን
አረንጓዴ ብጫ ቀይ ባንዲራችን ይዘን
እንደየ ባሕላችን አምሮብን ተውበን
ውብ ካባችንን ደርበን፤ በክብር እንገባለን
ሁሉም ዘር ተግባብተን በቋንቋችን ተቀኝተን
ዘፍነን፤ ዘምረን፤ ደንሰን፤ አስክስታችንን ወርደን
ሁላችን አንድ መስለን ሁላችን አንድ ሆነን

ተባብረን ተጣምረን፤ እህትና ወንድም፤ አባት እናት
ሆነን
የወይራ ቅርንጫፍ ዘንባባችን ይዘን
እንደ አሮሞዎች በዛጎል ተውበን
እንደ አፋሮቹ ሽርጥ አገልድመን
እንደ ትግሬዎች ሹርባ ተሰርተን
እንደ አማራዎች ጥበብ ሸማ ለብሰን
እንደ አደሬዎች ጀለቢያ አጥልቀን
እንደ ሲዳማዎች እንደ ወላይታዎች ግልድም አገልድመን
ልክ እነሱን መስለን
እንደ ጋምቤላዎች እንደ ሙርሲዎቹ ገመናችን ገልጠን
በከቡር ማዕዳችን በዙርያ ተቀምጠን
ቆርሰን ተጎራርሰን
በጋራ ቋንቋችን በስሬው ተጫውተን
እሰክታችን ወርደን
የጉራጌ ክትፎ በቆጮ ጠቅልሰን
ኤቦ ላላ ዘፍነን
እንደአርጋው በዳሶ በራሳችን ቆመን
በአግር አጨብጭበን
የኦሮሞ ምግብ ጨጨብሳችንን በልተን
አካም ነጥግ ጋሩማን ጨፍረን
ወገብ ሰወገብ ዙርያችን ተቃቅፈን
ወደምስራቅ ቆላ አፋሮች ዘንድ ሄደን
በከል አስጠብሰን በወተት አምገን
የማእዘን ድንጋይ ስመጥር አፋሮች

ከጥንት እስከዛሬ የኢትዮጵያ ቃፊሮች
ግመላቸው ሳይቀር አረንጓዴ፣ቢጫ፣ቀይ ባንዲራ
አፍቃሪዎች
በዚያው አቆራርጠን ወደ ሐረር ዘልቀን
ከአደሬዎችና ከሱማሌዎች ጋራ አንጥፈን ጎዝጉዘን
አጣን አጫጪሰን
ከልብ ተመራርቀን ይቅር ተባብለን
ጎንደር ጎጃም ዘልቀን ወሎ ደሴ ደርሰን
የአማራ ዶሮ ወጥ በያይነቱ ጠግበን
አንቺ ሆዬ ባቲ አምባሰል ተጫውተን
ከመከም ተቋድሰን አሀም፡አሀም፡ ብለን
ወላይታ ሄደን ኮንሶ ጋሞ ደርሰን
በዳጣ አጥቅሰን ጥሬ ሥጋ ቆርጠን
አይዞ ዶርዜ ዘፍነን
ዳሌአችንን ንጠን ወገባችን ሰብቀን
እመር፣ እንቸር፣ ብለን፣ እንደ ጥንቸል ዘለን
ወደ ሰሜን ተጉዘን እድዋ ላይ ሸለለን
የእድዋ ድል አስታውሰን እበባ አስቀምጠን
የአክሱም ሐውልት ጎብኝተን
የዓለም አንጋፋዋ ሴቷ ንግሥታችን፣ ሳባን እጅ ነሰተን
በድል የመጣውን ሀውልታችን አይተን
የትግሬዎች ምግብ ጥሀሎ ተጋብዘን
ሹሩባ ተሰርተን እግርና እጃችን እንሶሰላ ቀልመን
ላሎዬን ዘፍነን ከበሮ ደለቀን
ብሔር ብሄረሰቦች ሁላቸው አዳርሰን

ያኮረፉት መክረን በኢትዮጵያዊነት ታርቀን
ለምለሙም እገራችን በእኩል ተካፍለን
ቤት ንብረት አፍርተን በሀብረት ተሳስረን
በአህያ በበቅሎ በፈረሶች ጋልበን
ልጆች እስተምረን ሽማግሌ ጦረን
ከጓላ ተነስተን ሁሉንም እገር ቀድመን
ድል በድል ሆነን ድል በድል ጨብጠን
እንጀራ እየሰላን፣ ቡና እየጠጣን፣
ከሁሉ ኢትዮጵያዊ መተማመን ፈጥረን
እገር አስኩብረን እርሰ በርስ ተከባብረን
በሰላም በፍቅር በጎነት እንድንኖር እምላካችን ይርዳን።

<u>ትጉሁ ገበሬ</u>

የአገራችን ሕዝብ እንደምን ይራበው
እንዳንተ ያለ ጀግና ገበሬ እያለው
የግረሻው ጊዜ እፈር መገልበጫው
ቡቃያ ማብቀያው አረም ማስወገጃው
እሾህ እሚከላ ሥራ ሥር መንቀያው
ደመና ደምኖ የዝናቡ መምጫው
ምቹ የርሻ ጊዜ ወራቱ እሁን ነው
የማይረባውን አረም መንጥረው ቀጋውን
ገሰባውን አንጓሰህ እበጥረው ምርቱን
መልካም ፍሬ እንዲገኝ ጥሩ ዘር እንዲበቅል
እርሻውን አሳምር ባጭር ታጥቀህ ታገል
ጭንጫ ምድር ጠፍ መሬት አለሰልሰህ ፈንቅል

ከጥቂት ጀምረህ ኑሮህን አሻሽል
ዶሮ እያረባህ እንቁላል አስፈልፍል
ሰዎች መድሀኒት ጤና አዳምን ትከል
ለሕዝብ የሚጠቅም አዲስ ፍሬ አብቅል
በል እንግዲህ በርታ አምርት አደራህን
አራርሰው አረሰው አለስልስ መሬቱን

<u>መሪዎቻችንን ስንመርጥ</u>
ወኪሎቻችንን ስትመርጥ
አመዛዝኖ ይሁን በቅጥ
ተመራጩን ብቁ የሚያደርገው
ቀድሞ የሠራውን ሥራ በማመዛዘን ብቻ ነው
ሰወደፊት ሰማይ አርሳለሁ ዝናብ አዘንባለሁ በማለት
የሚያወራው ወሬ ከማምት ውስጥ አናስገባለት
የሠራውን እንጂ አሰራለሁ የሚለውን እጅግም
አንተማመን
ቀድሞ ባሳየው ተግባር እንመዝን
በፕሮፓጋንዳው ሳይሆን በምድር ላይ ባሳየው ውጤት
መሰረት
አይን ያየው ልብ ይፈርዳል እንደሚሉት

<u>ሞት ራሱ እንዲሞት</u>
ሞት እንደሁ አይቀር
ከፈጣሪ ከራሱ በስተቀር
አሰም አዱኛ ከንቱ

ዓለምን ያንቀጠቀጡ ሁሉ ሞቱ
በሳጥን በአፈር ተከተቱ
ከንፍ አውጥተው ከጠዋት እስከማታ ቢበሩም
ሰዘለዓለም እንደሆነ አይኖሩም
ታዲያ ሁላችንም እንድንተርፍ ምናለ እንዱ ቢሞት
የቀረነው እንዳንሞት
አስቲ እንበርታ በጸሎት
ፈጣሪ እሺ ብሎን ሞት ራሱ እንዲሞት

<u>ስልክ መደበሪያ ሆነ</u>
ዘመን ተሻሽሎ እጅግ ሲቀናጣ
ስልጣኔ በዝቶ ሰማየ ሰማያት ሸነቋቁሮ ሲወጣ
አገር አቋራራጭ ባህር ተሻጋሪ
ከሁሉ የፈጠነ አገልግሎት መጣ
ድንቅ ተብሰው ነበር ስልክና ቴሌግራፍ
እነሱን የሚያስንቅ ተከፈተ መዕራፍ
ጉዳይ ሰማስፈጸም ጓደኛ ለማፍራት
ንግድ ለማጧጧፍ ከሰው ለመግባባት
አገር ሰመትከፍት
ምሥል እያዩ ሰማውራት
ድምጽ ቀርጾ ለመላክ
ብዙ ጥቅም ሰጥቷል
ውጣ ውረድ አቃሏል
ስልክ ሌላ ጥቅምም አለው
መግባባት ለማይችል ቋንቋ ለሚያጥረውም ሰው

ራሱን ሰሚያፈቅር ለሰው ደንታም ሰሌለው
መልካም ፊት ማዞሪያ ማምለጫም ዋሻ ነው
ስልክ በደበሪያም ነው
ምኑ እሱ ብቻ አንደበት ሲያጥር
ነገር አልገባ ሲል ሲደድር ሲጠጥር
ስልክ ጥሩ መሸሻ ነው ራቅ ብሎ ሰመኖር
ነገር ግን በስብሰባም ሰአት በሆነ ባልሆነ
ቤተ ክርስቲያን መስጊድ በእድር ጊዜ ሳይቀር
መከታተል ጠፋ የአጀንዳው ቁም ነገር
ሰዉ ስልኩን ያያል ሁሉም ስልኩን ያካል
አንገት ራሱን ቀብሮ በጣት ይቆፍራል
ዝጉ እጥፉ ቢባል እዋጅ ግን ይሰማል
የብዙ አድማጭ ሀሳብ በስልክ ይወጠራል
በቫይበር በአይኤምኦ በፈስ ቡክ ተጠልፏል
ቴክስት ኢሜል ቪዲዮ ጠልፎታል
በየቤቱም ቢሆን ወዳጅ፣ቤተ ሰብ አላገናኝ ብሎ
የራሱ እድርጎታል ነጣጥሎ ከፋፍሎ

<u>ታሪክ አይረሳውም</u>
በአገር መኖር ትተን
በአገር መሞት ትተን

እንቅልፍ እረፍት አጥተን



ጉ�ዞ ገንዘብ ከፍለን ካገር እንጠፋለን እንሰደዳለን
እንዲህ ያለ ሽንፈት እንዲህ ያለ ውርደት
እንዲህ ያለ ውድቀት እንደመጡ መቅረት
በደቡብ አፍሪካ በእሳት የጋዩብን
በሜዲቴራንያን ባሕር ሰምጠው የቀሩብን
አክራሪዎች አርደው የፈጁብን
በሳውዲ አሬቢያ
በዱር በገደሉ ባውሬ የተበሉብን
በሰው በሳ ሰዎች የተበሰቱብን
በቤንዚን በጎማ የነደዱት በእሳት
በ2016 አመት ምህረት
በዜጎቻቸን ላይ የደረሰው እልቂት
የማይረሳ ነው የማይዘነጋ
ለኢትዮጵያዊነትና ለሃይማኖታቸው የከፈሉት ዋጋ።

<u>ራሳችንን እንምከር</u>
የአባቶች ጀግንነት ለዚህ አብቅቶናል
የትናንቱ ጥረት ለዛሬ እድርሶናል

ለነገ መነሻ መሠረት ሆኖናል
ካለንበት ሆነን ስናስብ የነገውን
ወቅቱ አሁን እኮ ነው እንሥራ ባጭር ታጥቀን
በዓለማት ዙርያ የተለራጨነው
ከውዲቷ አገራችን ላንወድ የወጣነው
በርትተን በመሥራት እንድናሸንፍ ነው
በትሕትናችን ሕዝብ ሁሉ ያፈቅረናል
ሁሉም በሩን ከፍቶ ኑ ግቡ ይለናል
ያፈራነው አድናቆት ጠረኑን ሳይለውጥ
የዓለም ኤኮኖሚ ሚዛኑን ሳይሟጥጥ
ሰርተን አጠራቅመን ራሳችንን እንምከር ራሳችን
እንለውጥ

<u>የክቡር አቶ ሠይፈ ታደሰ</u>
ርዕሰ ሴኔተር ሰይፈ አባታችን
ዋስ ጠበቃችን መመኪያ ጋሻችን
ግልጽና ርሕሩሕ ሰው ቸር መካሪያችን
እንደ ወላጅ አባት ሀቀኛ ዳኛችን
መክረውን ነበረ ስለ ሕብረታችን
እንድ ሳይ እንድንቆም ለውድ አገራችን
ተግተን እንድንጠብቅ ውርስና ቅርሳችንን
ሳስተማረን ሕዝብ እንድንከፍል ብድር
እኛም በተራችን ሄደን እንድናስተምር
ያስተምሩን ነበር ስለ አኩሪው ታሪካችን
በቀድሞ ታሪካችን ጀግና እንደነበርን

ዳር ድንበራችንን በትግል እንዳስከበርን
ኩሩ እንደነበርን ጨዋ እንደነበርን
ድሃ እንዳልነበርን ሓብታም እንደነበርን
ዛሬም እንደትናንት መሆን እንዳለብን
የጥንትና የዛሬ እያወዳደሩ
ክፉና በጎውን እያነፃፀሩ
ያጽናኑን ነበረ ኑሮ ሲሰለቸን
የቤተ ሰብ ናፍቆት ህመም እንዳይጥለን
የናት አባት ጠረን ፍቅር እንዳይጎድለን
አእምሮአችን ባዝኖ ኑሮ እንዳከብደን
ክቡር አቶ ሰይፈ እናት አባት ተክተው ምክር የሰጡንን
ማስታወሻ ሆኖ ከኛ ጋር ይኖራል
መንገድ ይመራናል ያበረታታናል
(ለሴኔተር ክቡር አቶ ሰይፈ ታደሠ ማስታወሻ የተፃፈ ጳጳስ ቴክላስ)

<u>አባይን አንክሰስ</u>
ሥራና ገመናህ በዚጎች አይን ሰናይህ
የምትወስድ እንጂ የማታመጣ ጉድ ነህ
ከወገን ይልቅ ባዕድ እየመረጥህ
ልጆችህ እየተራብን ንብረት ታሸሻለህ
ግዕድን ውህ ለም መሬት ታግበሰብሳለህ
ዛፎችን ገርሠህ ተራራ ደርምሰህ ለሰው ትሰጣለህ
ሌት ተቀን ተግተህ ባዕድ ትጠቅማለህ
ዘራፊነት ሙያ አድርገህ ታበረታታለህ
ከቶ ምን አይነት ዚጋ ነህ
አባይ ተከላሽ ነህ በዘራፊነትህ

እምነት በማጉደል አገርን በመክዳት
ያለሺዛ ድንበር አላብረህ በመውጣት
ትከሰሳለህ የሰውን ዘር በማጥፋት
ዜጎች አስጠምተህ ባዕድ በማጠጣት
ትከሰሳለህ ንብረት በማሸሽ ሰርቆት በማስተማር
ተሰማርቶ በመኖር በስረፋ ተግባር
የአገርን ምስጢር አሳልፎ በመሰጠት
ለቱርኮች፣ለግብፆች፣ለሱዳን ለአውሮፓውያን
ለምዕራባውያን መንገድ በማሳየት
ይፈረድብሀል የአገር ሀብት ዘርፈሀል
ይፈረድብሀል ዜጎችን ፈጅተሃል

<u>አዋሽ</u>

ታማኝ የአገር ልጅ ነው አዋሽ
በክፉም በደጉም ከወገን የማይሸሽ
የገበሬ የፋብሪካ የግድቦች መከታ
የዜጎች የእንግዳ የእፀዋት አለኝታ
አሉ ከሰዎችም ከወንዞች ታማኞች
በክፉም በደጉም ለወገን ደራሾች
እንደ አፄ ቴዎድሮስ
እንደ አፄ ዮሀንስ
ለአገር ለወገን ሟቾች
እጅ የማይሰጡ ዜጎች
ወደር የሌላቸው ጀግኖች

<u>** ምንድነው ራዕያችን</u>

የበለጸጉ አገሮች በሃብት የመጠቁት
ሕዋውን ሸንቁረው ጠፈር የደረሱት
ዘዴና ብልሀቱን ከወዴት አመጡት
እኛስ እንዴት እናድጋለን እንሻሻላለን
ለው ከደረሰበት እንዴት እንደርሳለን
ካልተቀራረብን በጋራ ካልቆምን በሕብረት ካልሰራን
ችግችም ብለን አንድ ላይ ካልቆምን
በጥቃቅን ችግር ተተብትበን ከኖርን
ካልተቀራረብን ካልተነጋገርን ካልተደጋገፍን
እቅድና ግባችን አብረን ካልነደፍን
ለልጅ ልጆቻችን ለውድ አገራችን አርቀን ካላሰብን
ለው ከደረሰበት እንዴት እንደርሳለን?
ሙስና እንዲጠፋ ቀጣፊ ካልቀጣን ለፍርድ ካላቀረብን
ከዘር ከሀይማኖት ልዩነት ውስጣችን ካላጠብን
ዓለም ካለችበት እንዴት እንደርሳለን?
ከሰዎች ካልተማርን በራሳችን ካልጣርን
በሕብረት ካልተጓዝን ጠንክረን ካልሠራን
ካልተደማመጥን ፍፁም ካልተቻቻልን
ካልተቀራረብን፡አገርና ወገን በጋራ ካልጠበቅን
እንዱ አንዱን ሲበድል ተው አታድርግ ካላልን
አብረን ተደርበን ተባባሪ ከሆንን መላሪያ ካቀበልን
ለጋራ ጥቅማችን መመካከር ካልቻልን
በሄድንበት ሁሉ በመሸበት ካደርን
ውርስና ቅርሳችንን ተንከባክበን ካልያዝን
የተፈጥሮ ሀብታችን ካልተንከባከብን
አንድ ዛፍ ላንተከል ብዙ ከቆረጥን

ደን ካቀጣጠልን አከሰለን ከሸጥን
ሀውልቶቻችን ሲፈርሱ፡ዝም ብለን ካየን
ውርስና ቅርሳችን እየለረቅን ከሸጥን
ካልተደግመጥን በሆነ ባልሆነ ከተጨቃጨቅን
በክብ ጠረጴዛ መነጋገር ካልቻልን
የተረከብናቸውን ለተተኪው ትውልድ በክብር
ካላስረከብን
እንዴት እናድጋለን እንበለጽጋለን
ለው ከደረስበት መቼ እንደርሳለን
ምንድነው ነው ራዕያችን
ወዴት ነው ግባችን
ምን ይዞ ጉዞ ነው ለልጅ ልጆቻችን

<u>ፖለቲካና ዘር</u>

አገር የሚመራ ለው ምረጡ ሲባል
ብቃት ያለው መሪ መቼ ይታየናል
የኛ ጉድ ብዙ ነው
ውስጡ ስንክሳር የሾላ ፍሬ ነው
ዓለም እንደሚያደርገው መሪ ምረጡ ሲባል
እውነተኛ መሪ መቼ ይታየናል
የዕጩ ስም ሲገለጽ ገና ሲዘረዘር
ይደቀንብናል የቡድን በሽታ ፖለቲካና ዘር

<u>አሳማና ዝሆን መቀለብ</u>

ልዩ ስም ለይመን መሪ እያሞገስን
ከለው ቁመት በላይ ከለማይ ላይ ለቅለን

ጡንቻውን አስፈርጥመን ልቡን አሳብጠን
ከምረን ከምረን ተራራ አሳክለን
አሰር ስም ለይመን ከለማይ ላይ ለቅለን
መብታችንን ሁሉ ወደን አስረከበን
ቁልቁል እንዲረግጠን እኛው አመቻችተን
በመጨረሻ ላይ ግራ እንጋባለን
የተከልነው ዛፍ መራራውን ፍሬ ለቅመን እንበላለን
ፍዳና መከራ ሰቃይ እንቆጥራለን
አባብ እናረባለን ዝሆን እንቀልባለን

<u>*ምስጢሩ ምን ነበር</u>

እጅ ለጅ ተያይዘው ተፋቅረው ሲኖሩ
ውበታቸው ደምቆ እንደዚያ ሲያምሩ
እንደ ብርሀን ፈክቶ ሰላም ውለው ሲያድሩ
እጥራቸው ተፈርቶ እንዲያ ሲከበሩ
ሕብረታቸው ፀንቶ ለጉድ ሲፋቀሩ
ያ ኢትዮጵያዊነት ምን ነበር ምሥጢሩ
የጥንቱ ኑሮዋቸው ቅመሙ ምን ነበር
እንዴት ቢያስተምሩ ይሆን የሃይማኖት አባቶች
እንዴት ቢያባድጉ ነው አናትና አባቶች
እንዴት ቢመክሩ ይሆን የአገር ሽማግሌዎች
ያን ህብረት ያን ፍቅር ዛሬ ላይ ብናየው
እለከ ትናንት በሰላም የኖረው
አሁን በጣም ታሞ፡ አልጋ ላይ ነው ያለው!

<u>የጎረቤት ያለህ</u>

ወዳጅ ሰፈርተኛ ከልብ ካልቀረቡት
ከቶ ምን ያደርጋል ጎረቤት ነው ቢሉት
ዕቃ ሲቸግር ብድር የማይኬድበት
እጥር ተደግፎ ወሬ የማያዋሩት
የውሰጥ የልብ ነገር ወሬ የማይነግሩት
አሜሪካን አገር በኩታገጠምነት ብዙ ዓመት ቢኖርም
ጎረቤት ጓደኛ አንድ እንኳን አይገኝም
ፈጽሞ አይቻልም ተማምኖ መጫወት
ቀርቦ ተቀራርቦ ሽንጎ መወያየት
ምስጢር መነጋገር ሻይ ቡና መጠጣት

<u>ምን ውጤአቸው ይሆን?</u>

አሜሪካን አገር ቤት በቁልፍ ቢጠበቅ
ማስቆም አልተቻለም አለ የሰው ሌባ አድፍጦ የሚነጥቅ
ሰወሬ አይመችም በጣም ግራ ያጋባል
ልጅ እዋቂ ሳይቀር ለሥራ እንደወጣ ሳይመለስ ይቀራል
ፎቶ ከፖስታ ቤት ተልኮ ሲመጣ
አፋልጉን የሚለው ብዛቱ ቅጥ አጣ
ይሄ ሁሉ ሲሆን፡ መንግሥት እንኳን ያልቻለው
ባሕር ወይስ ዘንዶ ምን ቢውጣቸው ነው?

<u>ጠላትን እናሳፍር</u>

በዚህ ወሳኝ ዘመን በዚህ ወሳኙ ወቅት
ለአገር ለወገናችን ተግተን እንሥራበት

መጨቃጨቅ ይቅር
መግባባት ይጀመር
እናምርት ተስማምተን
ሰምና ወርቅ ሆነን
አንድነት አክብረን ዜግነት ጠብቀን
ባንዲራን አማክለን
እናልማ አገራችንን ዛሬ ባጭር ታጥቀን
ግዴታ አለብን አደራ ወርሰናል
የትናንቱ ጥረት ሰዛሬ አብቅቶናል
በዛሬ ላይ ቆመን የነገን ሰናየው
ለመጓዝ መነሻ መሰረት ዛሬ ነው
ለውድ አገራችን ለሕዝባችን ብለን
አሁን ባጭር ታጥቀን እንጀምር ተነስተን
ምላሌነታችን በሁሉም አቅጣጫ
ሰላምና ፍቅር ሆኖ መገለጫ
የጥንት ታሪካችን ጥንታዊነታችን
ይገለጥ በሥራ ይገሰጥ በይፋ ይጠንክር ክንዳችን

<u>የአገርህ ድርሻ</u>

በዓል ስታከብር ብዙ ወጪ አድርገህ
ስትበላ ስትጠጣ ለታሬጥ ሰራስህ
ለልጆችህና ለቤተሰቦችህ ለዘመድ አዝማድህ
አስበህ ስትሰጥ ለዕምነት ሀይማኖትህ
ለአገርህ ድርሻ ስጥ ታረክ እንዳይወቅስህ
አመዛዝህ አኩል

ሳታደላ አካፍል

<u>የጥንቱ ኢትዮጵያዊነት</u>

እጅ ለእጅ ተያይዘን በፍቅር ስንኖር
ሕብረታችን ሰምሮ እንደዚያ ስናምር
ተከብረን ተፈርተን ቀን ውሰን ስናድር
ወራት ዘመናት በደስታ ስንቀምር
ዳር ድንበራችንን እንደዚያ ሲከበር
በሕብረት ነው እንጂ መች ሰየብኝ ነበር
ስናወዳድረው የጥንቱና የዛሬው
ርቀቱ ብዙ ነው
እንደ እንድ እንሰራ ውሃ ተዋህደን እንድ ሆነን
በዜግነታችን በጀግንነታችን ዓለም አስደንቀን የኖርን
ከእሪቱ ጊዜ አንስቶ እስከ ትናንትና ያለፍንበት ምስጢር
የጥንቱ ኢትዮጵያዊነት! ቅመሙ ሕብረት ነበር?
ብርታቱ ያ ነበር።

<u>እስቲ ልብ እንግዛ</u>

የኢትዮጵያ ልጆች ተግባብታችሁ ኑሩ
በራሳችሁ እንጂ በሌላ እትመሩ
የውጪ ተላላኪዎች ሰላም እይሰጡንም
ባእዳን እንደሆን ስራላቸው እንጂ ሰኛ አይበጁንም
ንጉሥ ፕሬዚዳንት ጠቅላይ ሚኒስትሮች
ብዙ ሀብት ያፈሩ የዓለም ባለፀጎች
ሰዎች ናቸውና እላፊና ጠፊዎች

ፍጡር ሁሉ ይሄዳል
ግዴታውን ይከፍላል
በፈጣኑ ባቡር ይመጣል ይነጉዳል
ሞት ይደርስበትና እዳውን ይከፍላል
ነውና የአምላክ ቃል
ስው እፈር ይሆናል
ከሱ ስለተገኘን
አፈር እንሆናለን
እኛ ግን ሞኞቹ! በኩንትራት ዘመን
መስማማት እያቃተን
የራሳችንና የአገራችን ጥቅም በከንቱ እያባከንን
ብዙ ዓመት ገደልን
የመከራ ዘመን የሰቆቃ ጊዜያት
በከንቱ ውዳሌ አለፉ ዓመታት
በሰደት አገር ሳይቀር እንጨቃጨቃለን
እስቲ ልብ እንግዛ የእንድ እናት ልጆች ነን
የእንድ እገር ዜጎች ነን
ሰጋራ ጥቅማችን
እንድ ላይ እንቁም እንደ አንድ ሰው ሆነን

<u>ወርቅ በእሳት</u>

አንድ ቀን ሀዘን ቤት ሰዎች በሞሉበት
እገሬን ሰደበች አንዲት ቀባጣ ሴት
እየተሳለቀች እንዲህ ብላ አፈዘች
ስቃ ሰው እሳቀች
እውነት እገራችሁን እማዜር ያፈቅራታል?
በማለት ቀጠለች የሚወዳት ቢሆን መጽሀፉ እንደሚል

ስምን ይቀጣታል በድርቅ ይመታታል?
እየተዘባነች ጥያቄ እስመስላ
ብዙ እላዘነች ምላሰዋን ጎልጉላ
ማን መሰለቻችሁ እንደዚያ ያስችን
እኛው ያሳደግናት የንጀራ ልጃችን
ፊትዋ ሰው የሚመስል ያቺ የሌሊት ወፍ
እገር የምትሰድብ አንዳሻት የምትዘልፍ
አልገባትም አንጂ ካሰበችው በቅጥ
መጽሀፍ ብታነብ አዋቂ ብታደምጥ
እግዚአብሄር ሲፈትን የሚወደውን ሲመርጥ
ስሚያፈቅረው ነው ፈተና የሚሰጥ
የእስራኤል ሕዝቦችን በፍዳ በአሳር ብዙ ፈተናቸው
ሰግብጻውያን ስጥቶ ባሪያ እደረጋችው
የፈጣሪ ወዳጅ ኢዮብንም ያስቧል
ሀብቱን ሁሉ ወስዶ በቁስል መቶታል
ጻድቃን ስማዕታት በፈተና አልፈዋል
መጽናት ያስፈልጋል ዕምነት ያስፈልጋል
ወርቅ ወርቅ መሆኑን በእሳት ይፈተናል

<u>ድሮና ዘንድሮ</u>
እስቲ እናወዳድረው የዛሬና የጥንት
የሀዘቡ ጀግንነት የሕዝብ እንድነት
ኧረ የት ደረስ ያ ኢትዮጵያዊነት
በራስ መተማመን ያገር ፍቅር ስሜት
የጥንት ስልጣኔ የነበረን ሀብት
የነበረን ክብር የነበረን መንግሥት
የአገራችን ርዝመት የእገራችን ስፋት
የነበረን ብቃት የነበረን ሥርአት
ራሳችንን እንጠይቅ ውስጣችን እንመርምር

በዚያው ብንቀጥል ኖሮ የት በደረሰን ነበር

<u>የእግር ኳስ</u>
አስታዲዮም ታየኝ
ካታንጋ ምስግር ተራ ጥላ ፎቅ ትዝ አሰኝ
አይ ምስግር ተራ
ሕዝብ ሲሮህ ሲያቅራራ
ታዳሚ ሲጠፋጠዝ
ለውድድር ክኪስ ሲመዝ
ቆሎ ሻጮች ሳንድዊች ሻጮች
ማስቲካ ክረሜላ ሲጋራ አዙዋሪዎች
የመሀል ዳኞች አራጋቢዮች ኳስ አቅራቢ ልጆች
የእግር ኳስ ቡድን ተጋጣሚዎች
አየር መንገድ ጊዮርጊስ መቻል
ቡና ገበያ መብራት ኃይል
እሚድላ ያሸንፋል
ክርክሩ ቱክክሩ ግሎ ይጠፋል
ሁሉ ይጮኃል ያንቧርቃል
ኳስ ባየር ይለጋል ፊሽካ ይነፋል
ቁጭ ብድግ ይባላል! ቧልት ይመረውራል
አንዱ ይላደባል ሌላው ይተርባል
ይህ ነው ጨዋታ! ይህ ነው ጨዋታ
ቡድኔ ይረታል ብሎ ሁካታ
ኳሱ ሲያበቃ ወይ አሸንፈ አለያም ተሸንፈ ብሎ መጣላት
ምክንያት ፈልጎ ዞሮ መጠጣት
ስክሮ መጨፈር
መሸታ ገብቶ እስክስታ መውረድ ግጥም መደርደር
ቅዳሜና አሁድ ደርሶ ሲጠጡ ማደር

<u>ሃያሉ ፍቅር</u>

በልጅነት ቋንቋ በወጣቶች ባህል
በለግሳጋዎች ብሂል
በትምህርት ቤት ዙሪያ ፍቅር እንዲህ ኖሯል
የፍቅር ስንኞች በፍቅር ጣዖራዎች
ይቋጠሩ ነበር
ይገጠሙ ነበር ይነበቡ ነበር
ፍቅሬ ግር ወተቴ
አንጀት ኩላሊቴ
ፍቅርሽ እጅግ ራበኝ
ጥማቱ ገደለኝ ናፍቆትሽ ገደለኝ
ሎጋ ሰውነትሽ የንብ ንግስት ሽንጥሽ
ብርቱካን ነው ጣምሽ ወተት ይመስላል ጥርስሽ
ብቅ ብሰሽ ታይኝ ስርቅ እድርገሽ እይኝ
ብቅ ብሰህ ጠይቀኝ ስርቅ እርገህ ጥለፈኝ
የራስህ እድርገኝ
ወንዶች ከሴቶች ሴቶች ከወንዶች ጋር
መግባባት ልምድ ነበር
ግጥም መሰዋወጥ መጻጻፍ ወግ ነበር
እስተማሪ ሲያስተምር፡ ሰርቆ መመላከት
ግጥም ደብተር ውስጥ መከተት
እንዲያ ነበር ግጥሙ
እንዲያ ነበር ጣዕሙ
የወጣትነት ዘመን የትምሕርት ቤት ፍቅር
እንዲህ ያለ ነበር
ተማሪ ይጻጻፋል
ወጣት ይሳሳማል ዘመድም ይሳሳማል
መሳሳም ይጠቅማል
ስው ለሰው ያግባባል መጣጣም ይፈጥራል

ፍቅር ያዳብራል መቃቃር ያርቃል
በፍጥነት ያግባባል ልብ ያቀራርባል ልብ ያስተሳስራል
ስዎች ይሳሳማሉ ይገባበዛሉ
ዘመድ አዝማድ ይሆናሉ
አብረው ይኖራሉ፤ ይከባበራሉ፤ ይተማመናሉ
ጊዜ ያሳልፋሉ፤ ዘመን ይቆጥራሉ
እንዲህ የሚያደርገው
እግዚአብሄር የሠራው ሃያሉ ፍቅር ነው

<u>ሕዝብ ይጠብቃል</u>

በስዎች ህሊና በዓለማችን ዙሪያ
ፍቅረ ንዋይ በዝቶ ተንኮል እያደራ
ርካሽ ዝናና ገንዘብ ለማግኘት ምን እንደሚሠራ
በስብስባ ስፍራ በሀይማኖት መድረክ
ከአጀንዳ ውጪ ከመጽሀፉ ውጪ ምን እንደሚሰበክ
ፈጣሪን አለመፍራት ሀቀኛ አለመሆን
አደራን መዘንጋት ከቶ ለምን ይሆን
ቃሉን ብንከተል በእውነት ብናተኩር
የለው ልጆች እድገን የት በደረሰን ነበር
ከታላላቅ ሰዎች ከአገር መሪዎች
ከሀይማኖት አባቶች
ከአገር መሪዮች
ሕዝብ ይጠብቃል ዕውነት ነገር ማየት
እውነት ነገር መስማት።

<u>መንግሥትም እንደሰው</u>

የአገር መሪዎች በዓለም መድረኮች
በሁሉም ስፍራዎች
ይፈራረማሉ ይበጻደራሉ

ይለዋወጣሉ ገዝተው ይሸጣሉ
ገንዘብ ይመሰዳሉ ወይ ያባክናሉ
የነገሮች ሂደት ለሚከታተል ሰው
የተሰጠው ገንዘብ የወሰደውን ብድር
አልከፍልም በማለት ይፈጥራል ክርክር
ዛሬ እንደሚታየው መንግሥትም እንደሰው
ሂሳብ ሲጎድልበትና መክፈል ሲያቅተው
ድምጹን አሳምሮ ይወጣል ሊለምን
ድራማ ሊሰራ ትርኢት ሊከውን
በጣም የሚገርመው
መንገሥትም እንደሰው ለካስ ውሸታም ነው

**ሱሲ በአሜሪካ ጉብኝት

የዓለም ሕዝብ ቅርስ የሆነችውን ሉሲ (ድንቅነሽ)
ከኢትዮጵያ ወደ አሜሪካ ለጉብኝት መምጣቷ
ምክንያት በማደረግ በዓለም የዜና ማሰራጫ በተነገረ
ጊዜ እ.ኤ.አ. በሰኔ ወር 2004 ዓ.ም ፀሐፊው ቁሪስት
ቅርስ ወዳለበት አገር ይሄዳል እንጂ ቅርስ ቁሪስት
ወዳለበት እንዴት ሊሄድ ይችላል ከሚል ሐሳብ በመነሳት
የጻፈው ማስተወሻ ነው። **********
ይድረስ ለውድ እናቴ ድንቅነሽ
አካላቴ ሉሲ እያት ቅድመ አያቴ
አሻራና ግተብ የጥንቷ እናቴ
የሰው ልጅ ሁሉ ምንጭ የኔም ማንነቴ
የአፋሯ ተወላጅ እቴ እመቤቴ
መታጨትሽን ሰማሁ እንዴት ይለማሻል
ወግ ማዕረግ ልታዪ ቪዛ ተሰጥቶሻል
አራት ሚሊዮን በመን1 ካገርሽ ሳትወጪ
ሽርሽር ሳያምርሽ ብልጭልጭ ሳትመርጪ

እልቦ መቀነትሽን ማተብ ሳትሰውጪ
አገር ስታቀኚ ድንበር ስትጠብቂ
ምንም ሳይበግርሽ ከወንዝሽ ሳትርቂ
የልጆችሽ ትግል በትዝብት ስታዪ
የነገሥታት ለውጥ በዛ አነሰ ሳትዪ
በባዕድ ወረራ በዳር ድንበር ጉዳይ
በበረሀ ኑሮ መከራ ስታዪ በዋሻ ተቀምጠሽ
በጉድጓድ እየዋልሽ በዋሻ እያደርሽ
ዜግነትን መርጠሽ መስዋዕትም ሆነሽ ኢትዮጵያን
ጠብቀሽ
ያን ሁሉ ቀውጢ ወቅት ችለሽ አሳልፈሽ
ብርቅ ብር እምባርሽ በጽኑእ ጠብቀሽ
ከአገርሽ ጀግኖች መርጠሽ ማግባት ትተሽ
እስከዛሬ ድረስ1 3.5 ሚሊዮን ዘመን1 ባለሽበት ነበርሽ
ሕግሽን ጠብቀሽ ሥርአት በማስከበር
ኑሮ ሳትስለቺ1 ስደት ችላ ብለሽ ባገር ኖረሽ ነበር
ዛሬ በምን ምክንያት አሜሪካ መጓዝ መንሽርሽሩን
መረጥሽ
ለምን እባበሉሽ እንዴትስ ተስማማሽ
ነገሩ ምን ይሆን የድግሱ ምስጢር የስሞኑ እይሾሽ
ልትመለሺ ነው ወይንስ ሊያስቀሩሽ
ሰውን የሚያጠምደው ውጠህ ስልቅጥ እገር
ጉብኝት ተጠራሽ ፈረሙ ሊወስዱሽ ፈረንጅ ሊያጋቡሽ
እጅግ ጠርጥሬአልሁ ሆዴም ባርባር አለው
በዚህ አይነት ዘዴ ቅርሶቹ የቀሩት በዘዴ ተወስደው
በረቀቀ ዘዴ መንነው የቀሩ1 የሄዱ ተዘርፈው
እጅግ ብዙ ናቸው
ድንቅሽ ጠርጥሪ
ወጥተሽ እንዳትቀሪ

ሲጋቴን ልንገርሽ አምሳያሽን ስለው
አንቺን መሳይ ስርተው ምትክሽን ልከው
አንቺን አስቀርተው
ብር አምባርሽን ወስደው ዜግነትሽን ሰውጠው
ዲቃላ አስረግዘው የነሱ ሊያደርጉሽ ነው
ይሄኔ ግን ያውቃል
ሰው ሰራሿ ሉሲ ተስርቶ ተቀምጧል
ተጠናቆ አልቋል
አዋዩ ነግርኖል
ሉሲ አትመስሰም አበቃች ብሎኛል
እመቤቱ ሉሲ በይ ደህና ሰንብቺ
ጥናቱን ያድልሽ በርቺ ተበራቺ
አጥብቀሽ ታገዪ ክቶ እንዳትረቺ
የኢትዮጵያ አምላክ ይጠብቅሽ አሜን
ያብቃሽ ለአገራችን
[ዳላስ ቴክሳስ በ10/24/2004]

ትዳር በጥቃቅን ችግር

በትዳሩ ጎራ የዘመናት ወዳጅ አንጡራ ጓደኛ
ክፉና ደግ አይተው ያለፉ ፍቅረኛ
ቤት ስርተው በልጽገው ልጅ ወልደው የዳሩ
ሃያ አመት አርባ አመት ዘመን ያስቆጠሩ
ከሁር የሆነውን የጋብቻ ምስጢር
አርመው ከትኩተው ያሳደጉት ትዳር
መስዋዕት በመሆን ያበቁት ሰክብር
ባልና ሚስት ሆነው ጥረውና ግረው ያዳበሩት ፍቅር
መቻቻል አቅቶአቸው ሲንዱት ይታያል በጥቃቅን ችግር
ስርቶ ስመጠቀም ነግዶ ስመክበር
ልጅ ወልዶ ስመዳር

መግባባት መስማማት ወሳኝ ነው ስትዳር
የገሬ ወንዶች የባለባሕል ልጆች
ጥቁር ግስላዎች ዥጉርጉር ኑብሮች
ዳልጋ አንበሳዎች
የአገሬ ሴቶች እናት ወይዘሮዎች
ጠይም አንጀራዎች ወለላ ጣዝማ ማሮች
የፈረንሳይ ሽቶ የጥቅምት እሸቶች
ምክሬን ተቀበሉኝ ተባብራችሁ ኑሩ
ሁሌ ተረዳዱ ጠንክራችሁ ሥሩ
የአገሬን ቡልኮ ጋቢ ደርባችሁ
አንተ ትብስ አንቺ ፍቅሬ ተባብላችሁ
ተግባቡ ተግታችሁ
ነፋስ እንኳ እንዳያልፍ በመካከላችሁ
ወልዳችሁ ክብዳችሁ ኑሩልን አደራ
ጥምረታችሁ ይስመር እንደ አብርሀምና ግራ

ስውጭ በገባሮች

አትበክሉት ውሃው
አትግደሉት አሳው
አታቃጥሉት ሳሩን አትመንጥሩት ደኑን
አትከልክሉን ዝናብ በድርቅ አትጨርሉን
ሩዛችሁ ይቅርብን ጤፍና ገብስ አሉን
ራሳችሁን ቻሉ አባካችሁ ተዉን
የኛንም አትንኩ የናንተንም አትስጡን
አገራችን ሰም ነው ብዙ ማዕድን አሰን
የወርቅ እንቁ የአልማዝ አገር ነን
ችግር አታምጡብን
ራሳችሁን ቻሉ ጣጣችሁ ይቅርብን
መድሃኒት አትርጩ አፈር አትበክሉ

ባሕር አታቋርጡ ድንበር አትጣሱ ራሳችሁን ቻሉ
ጭቡጦ ይዛችሁ አሻሮ አትጠጉ
እኛም ባገራችን እናተም እዚያው እርጉ
የእገራችን ሰርዶ ይሁን በራሳችን
ድንበር ተሻግራችሁ ዘር አታበላሹብን
ኬሚካል እትንቱ ቅንቅን አትርጩብን

<u>ይድረስ ለወ/ሮ ዓለም ፀሐይ ወዳጀ</u>
<u>ከወ/ሮ ዓለም፡ፀሓይ ወዳጀ፡ ግጥም መጽሐፍ በከፊል የተተነጨበ</u>
"የግታ፡እንጀራ ሰጠኝ
.የጠዋት እታሰመርጠኝ
ዘግይተህ በኋላ እጊጠኝ
.ግታ በከብሬ ደብቀኝ
.ከሰው ቤት እንተው አርቀኝ
.አደራ ጌታዬ አደራ
.እትንሳኝ የግታ አንጀራ.."
<u>የፀሐፊው፡ምላሽ፡</u>
ዓሰም ፀሐይቱ ብርቅዬ ልጃችን
መላ ካንቺ ሞልቷል አኛንም እትርሺን
ብርሃን፡ሙራ፡ሀገሽ፡አባክሽ፡ጉልበት ስጪን
የንጋት ኮከብ ሀገሽ እስቲ መንገድ ምሪን
ራት ስትጠይቂ ቁርስ ምሳ ትዝ እሰን
ሲበላ አየን እንጂ አኛስ መቼ አገኘን
የግታውንማ በእንቅልፍ ይታሰፋል
የጠዋት የቀን ችግር እንዴት ይዘሰቃል
አምላክ በጥበቡ ምላሽ እንዲሰጠን
የሁላችን እናት እትዮጵያም ጨምረን
በጋራ እንጠይቅ በሕብረት አንድ ሆነን
ይብቃ፡በቃ፣ብሎ፡አንባችን፡እንዲጠርግልን

የቀንም የግታ እንጀራ እንዲሰጠን
ከውርደት ከሰደት ከሞት አንዲያድነን
ቁጣውን በምህረት፣ እንዲለውጥልን
ደመናው በዝናብ፣ እንዲቀይርልን
ፀሐይ፡አንዲያወጣልን
ለኢትዮጵያውያን ሁሉ፣አኩል እንዲያበራልን
በሕብረት እንጠይቅ አንቺም አኛም ሆነን
አጅግ፡ተወያይተን፡በጣም፡ተቀራርበን፡
እንደ እንድ ሰው፡ሆነን
ሁላችንም፡ቆመን፡ቀን፡ተሌሊት ጮሽን
እሚን፡ይሁን፡ጀባ፣
እግዚአብሄር ያድምጠው፣ያንቺም የኛም እንባ
የጎደሰው፡ሞልቶ፣ያሻነው፡አግኝተን፣በክብር እንድንገባ።
እግዚአ፡እቤት፡እቤት፡አስባት ኢትዮጵያን
እጇን፡ዘርግታለች፡እኛንም እትርሳን
ቁርስ፡ምሳ፡እራት፡ሰጠተህ፣ሁሉም...
አደላድለህ፣ላገራችን፡አብቃን፣
.እሚን፣ አሚን፣ እሚን።

<u>ይድረስ ለሎሬት ፀጋዬ ጻግማዊ (የንጉን ያየ ፈላስፋ)</u>
ሎሬት የለው መቅድም ተዋጊ በብዕር
እንደበቱ ርቱዕ ሰምና ወርቅ ምስጢር
የእንግሊዝ ሼክ እስፒር፣የግሪኩ ሆሜር
ደራሲም ፈላስፋ የቅኔ መምሕር
የቀለም አባታችን ማር የሚያዘንብ ሰው ነበር
ኢትዮጵያን እጽናኗት አልቅሳ ሸኘችው
ሀዘኑ መሪር ነው ልጅ የሞተበት ሰው

ማን እንደሱ ሊሆን የልቧን የሚያደርስላት
በልሳነ ቀሰም በልሳነ ብአር የሚሟገትላት
ኢትዮጵያን እግዜር ያጥናት
የአቡነ ጴጥሮስ ልጅ ራሱም ጴጥሮስ ነበረ
በተግባር በሥራው እንደሱ የኖረ
ጴጥሮስና ሎሬት ሱሳቸው አንድ ነበር
ሰባንዲራ መሞት መሰዋት ለአገር ፍቅር
ተሳክቶላቸዋል ግባቸው ያ ነበር
ፀጋችን እንነጋገር አስቲ እንወያይ
በመሄድሕ አዘንን ምርትህን ሳትሰበስብ ፍሬውንም ሳታይ
አልሰማንህም እንጂ ነግረኸን ነበረ እጅግ አበክረህ
በዘር በሀይማኖት እንዳንከፋፈል በጥብቅ አስጠንቅቀህ
አዎን እንዲህ ብለህ !!!!
“ሞስሊሞች ነን የምትሉ እንደ ዑመር ሰመተር
በኢትዮጵያዊነት ታጠቁ”
“ክርስቲያኞች ነን የምትሉ እንደ ጴጥሮስ ንቁ”
“ተቃዋሚዎች እባካችሁ በአንድ አንደበት ተናገሩ”
“በተናጠል ዲስኩር ሕዝቡን አታደናግሩ” [ከሎሬት
ያልታተመ ጽሁፍ የተወሰደ]
ስለሀብረት ስለፍቅርም አስተምረህ ነበር
ያውም በራስህ ድምጽ በራስህ አንደበት
ሳንካ በሌሰበት
“እሳት አንሆን ወይ አበባ
ባከነች ልጅነታችን ዕየቃተትን ስናነባ
ሕብረት ፈራን፤ ፍቅርን ፈራን፤

የፍቅር አምላክ በረቂቅ ያሰበሰንን ፍቅር ነሳን፤
የነፍስን አንደበት ዘጋን”
[አምን ሎሬት ዛሬም ያው ነን
አሰን ፍቅርን እንደፈራን]
ዛሬም እንደ ትናንትና እንዳለን አለን
ሰብዙ ዘመናት ምክር አልሰማ ብሰን
ጊዜአችን ተቃጥሎ እኛም አየተቃጠልን
እንሆ አሰን፤ በዘር በጎሳ ተደራጅተን፤ የጎሪጥ እየተያየን
ሎሬት ስለ ወል ቤት ስታስተምረን
ከቶ አይረሳንም እንደዚያ ያልከን
“ወሎ ሕብረት”
“ወሰጋ ታላቅ ሕብረት”
“ወልቂጤ፤ ወሊሶ፤ ወላይታ፤ የዕውነት አንድነት”
“ወልመራ ወልንጪቲ” ወዘተ ብለህ ነበር
ታዲያማ ወሎንም ውሎንም ረሳን
አለም ሊቀራረብ አኛ ዘር በዘር ላይ ዘራን
በመካከላችን ትልቅ የግንብ አጥር ሰራን
አሮሞ፤ አማራ፤ ትግሬ፤ ጉራጌ፤ ሲዳሞ ተባባልን
ሰዚህማ ማን ብሎን
በኔ ይበልጥ በኔ ይበልጥ ተጃጃልን
ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለውን አጣጣልን
ታሪክ ነጋሪ ምስጢር አዋቂ ጠላን
የምንገናኝባቸውን ድልድዮቻችንን አፈረሰን
የገዛ አርስታችን ከራሳችን ጋር ተካፈልን

ብዙ ባንዲራዎችን ብዙ ግድግዳዎችን ሠራን
ብዙ ሠራዊት እቋቁመን እርስ በራሳችን ተዋጋን
ፈሪ ሆነን ፍቅርን ፈራን ሕብረትን ፈራን
አምን አንዳልከው የነፍስን አንደበት ዘጋን
እየቃተትን ስናነብ ባከነ ልጅነታችን ..
ያሳዝናል ሞኝነታችን
አሰቲ መጥተህ እየን ብቅ ብለህ!
ለአንድ እፍታ ከሙታን መንጋ ተለይትህ
የቱን ያህል መጃጃላችንን ታየዋለህ።
ክልል እይናችንን ከልሎናል
ዜግነታዊ ዝምድናችንን አሰረስቶናል
በራስ መውደድ አስምቦናል
አንዳንዱ ነቅቷል አንዳንዶቻችን ተኝተናል
ትንቢትህ ይፈፀም ዘንድ ጀምሯል
ወይ ይፈርሳል ወይ ይፀናል
በብዙሀኑ በገዳ ወይ በሸንጎ ይዳኛል።
ገዳ ካ አዳ የእግዚአብሔር ሕግ ነው ያልከው ይረታል
የእግዚአብሔር ቃል ያሸንፋል
ምቼም ያልተናገርከው የለምና
ኢትዮጵያ የፍጥረት ሁሉ ምንጭ
የለው ልጅ መገኛ፣ የመጀመሪያ ሥልጣኔ
መፍለቂያ ናት ብለህ አስጠንተሽናል
"ካም ቱ ኤዮፕ" ኤዞጵ በማለት ያሰፈርከው
"ዘ ኤርክ ኦፍ ኤዮፕ ብሳክ ፍሎሶፈር...

Very little is known very little
studied so far"
ብለህ .በዛ በርቱእ አንደበትህ.....
(ኤት ኦፕ ግለት በጥንታዊው የኩሽ ቋንቋ
ኢትዮጵያ ማለት ሆኖ ትርጉሙም The
upper throuth (ትልቅ እውነት) ማለት
እንደሆነ ነው ያለመርከበት..
ነበረ ልበል እንጂ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት
እንደ ሙሴ ጽላት ምስጢር የነበሩበት
እንደሀዋርያት በመጻፍ ቅዱስ የተነገሩበት
በዓለም ዙርያ የተከበሩበት
እንደ ያሬድ ዜማ ረቂቅ የሆነበት
ኢትዮጵያዊነት እንደ ዛሬ ሳያሳፍር
አንደ ዛሬ እንደ ሬት ሳይመር
ሎሬት ፀጋችን ሰምና ወርቅ ቅኔነታችን
ረቂቅና ግዙፉ ከብራችን
እንደ ነብር እንደ እንበሳ ምነሳችን
ይህ ሁሉ በልባችን እንደ ፃፍከው ዘለዓለም
እናስታውስህን

<u>ይድረስ ለፕሮፌሰር መሰፍን</u>

ታጋይ፣ምሁርና ከቡር ፕሮፌሰር
የመብታችን ጋሻ የቀለም ወታደር
ለኛ ቆመው ከሦስት የአገር መሪዎች ሲታገሉ
ብዙ ቢጎዱም ሁሉንም አሳልፈው እርስዎ በሕይወት እሉ

ስለምናምንዎ ወኪል ነገረፈጅ እንዲሆኑልን
ዕድሜና ጤና በሰሬው ይስጥልን
ማቱግላን ያድርግልን
ተቆጥሮ የማያልቀው አገራዊ ውለታዎ
ፈጣሪ አምላካችን አሱ ይከፈልዎ
አምባ ገነኖችን፣ ሥልጣን ልቀቁ ብለው ከሚለምኑልን
በሃይል ከዙፋናቸው ላይ ፈንቅሰው እንዲጥሉልን
የዝሆን ዋንካሬ የአንበሳ ልብ ሰርስዎ ይስጥልን
ፕሮፍ ጥያቄ አለኝ፣
ይቅርታ ያድርጉልኝ
እርስዎ እማራ ሆነው አማራ ከሌለ
ስሌቱ አልገባኝም የሂሳብ ችግር አለ
አማራ አለመኖሩን በጥናት ደግፈው በጽሁፍ ካስቀመጡ
በጥባኤ ፊት፣ ቀርበው ካረጋገጡ
ታዲያ እርስዎ ከየት መጡ?
አማራ የሚለው ቃል ከኛ ከጎደለ
አማራ ከሌለ ኢትዮጵያስ የት አለች አበሻስ የት አለ
ዋናው ብሔር ሲገደፍ ሂሳቡ ተምታቷል
ኢትዮጵያ ያለአማራ እንደምን ይሆናል
ይኸ ነገር እጉል ነው፣ ቢተዉት ይበጃል
በአማራ ጉዳይም፣ ከአበሻ ጋር ከሚጣሉ
ሀሳብዎን ስውጠው እማራ፣ በቦታው አለ ይበሉ
ጎንደር፣ ጎጃም፣ ወሎ ሄጀ፣ አገኘሁት ይበሉ
የነ ዶናልድ ሲበን ፈሊጥ፣ ግራ ስላጋባን
ግሬ ላይ እናቁመው፣ አናራግበው ይብቃን
እፈታሪክ ታሪክ ትተን፣ ታሪክን እንከተል፣ እውነት እንከተል

እማራ አማራ ነው፡ ሃይማኖት ነው አንበል
ከዚህ በተረፈ፣ የእርስዎ ውለታ፣ ብዙ እዳ አለብን
ከጥንት እስከዛሬ ብዙ ስለመከሩን ብዙ ስላለተማሩን
ዕዳችን ብዙ ነው እንዲያው በደፈና አምላክ ይክፈልልን
ከታላቅ ምስጋና ጋር፡እግዚአብሔር ይስጥልን

<u>ይድረስ ለሎሬት ሚትር አፈወርቅ ተክሌ</u>

ሠላም ይሆንልዎ መሬት ይቅለልዎ
የስግይ ቤት ይመችዎ
እንደ አውሮፓውያን የትምሕርት ቤት ጓደኞችዎ
ኢትዮጵያዊ በመሆንዎ እርስዎማ መች ተመቸዎ
ንጉሡም ንጉሥ እላሳመረም ሲሉ
እብዮተኞችም አብዮቱን አልሳስም ሲሉ
ባለጊዜዎች በሥራዎ ላይ ጉድፍ ጣሉ
ሆኖም አገርና ሕዝብ ከቀረጹ የሚበቃ ይመስለኛል
በዚህ መስክ የሠሩት ታሪክ ይመስክራል
ነቢይ በእገሩ መች ይከበራል
ላስተዋሰ ለአገርዎ ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል
በልጅነትም የአካል ጉብርም ከፍለዋል
በዕውቀትም እስከ መጨረሻ ለእገርዎ ቆመዋል..
እናትዎ ኢትዮጵያን ኩለውና ሞሽረው አሳውቀዋል
የቆንጆዎች ቆንጆ አድርገው ስዓለም ገበያ አቅርበው
ረተዋል
ከቁመታ ሳታጥር፡ ከጎኗ ሳትከሳ ኢትዮጵያን ሠርተዋታል
በሚሊዮኖች ዶላር አልሸጥም ብለዋል

ልብ ይበል ልብ ያለው
ልብ ይግዛ ልብ የሌለው
ከፋኝ ብለው ላይሰደዱ
ለመዋዕለ ንዋይ ላያንበድዱ
በአገር ኖረው በአገር ማረፉን የወደዱ
የዓለም ሎሬት ሜትር አፈወርቅ ተክሌ
የልበ ሙሉ የኢትዮጵያዊነት መርሐ ምግሌ

<u>መዝሙር</u>
ኢትዮጵያ አገራችን ኢትዮጵያ እናታችን
የሰው ልጆች ምንጭ መመኪያ ክብራችን
እሚዩ ኢትዮጵያ የወርቅ ካባ ልበሽ
የአበሻዎች አገር የጀግኖች እናት ነሽ
ባያት ቅድመ አያቶቻችን ደም ስለተከፈለብሽ
ብዙ ጀግና ከፍለሽ አስከዛሬ ስለኖርሽ
ዛሬም በኛ ጊዜ ማንም አይከጅልሽ
የሚጠቅም ዜጋ ልጅ ይወለድብሽ
በነፃነት ኑሪ አምላክ ይጠብቅሽ
ዛሬም እንደጥንቱ ዳግም ቀን ይውጣልሽ
አብቢ ለምልሚ በልጆችሽ ኩሪ
ጠላቶሽ ይጥፉ በነፃነት ኑሪ
እንደጥንቱ አምሮብሽ የአፍሪካ ችቦ አብሪ
ኢትዮጵያ በልጽገሽ ሰላም ፍቅር ይንገሥ
ለምድርሽ ለልጆችሽ ደስታ ይዳረስ
ሁሉም ለብሶ ይመር ሁሉም ጠግቦ ይደር
ያለአንዳች ገደብ ሉዓላዊነትሽና አንድነትሽ ይክበር

<u>ተፈጸመ</u>

አምላኬ ሆይ አስጀምረህ ስላስጨረስከኝ አመሰግንሀለሁ። ለተፈጠርኩበት አላማም አንድኖር በቸርተትህ እርዳኝ።

<u>አበርክቶት</u> ለአገራቸውና ለሕዝባቸው ፍቅር ሲሉ ሁለት አንጋፋ ልጆቻቸው አጋዝ ወልዴና አይሠፂያር ኃይለማርያምን ይዘው ማይጨው ጦር ግንባር በዘመቱው ከጣሊያን ጋር የተዋደቁና በኋላም ለውለጥ አርበኞች መሸሸጊያና መተላለፊያ በመሰጠት ከፍተኛ አገራዊ ግዴታቸውን ለተወጡት አባቴ ፊታውራሪ ገንበዞ [ንበዜና] እንዲሁም በእምለቱ የጣሊያን ወረራ ዘመን በውስጥ አርበኝነት በመላተፍ ለአርበኞች ስንቅ፤ ትጥቅ፤ የመገበያያ ጠገራ ብር ገንዘብና መረጃ በመለጠት ለረዱት ለወላጅ እናቴ ወይዘሮ ተዋበች ገብረየለና ለእክስቴ ወይዘሮ ማሚቴ ገብረየለ ይህ መፃፍ ማስታወሻ እንዲሆናቸው አበርክቻለሁ።



1



2

<u>ምስል</u>
1/አባቴ ፊታውራሪ ገንበዞ [ንበዜ] እንላዋና 2/ እናቴ ወሮ ተዋበች ገብረየስ።

<u>ምስጋና</u> የቤተሰብ ጊዜያቸውን መስዋዕት በማድረግ ለረዱኝና መልካም የሥራ መንፈስ ላመቻቹልኝ ባለቤቴ ወይ/ሮ የምሥራች ተስማ፤ ልጆቼ ዮናኤል ይርጋዓለምና አልፋ ይርጋዓለም፤ እንዲሁም

በምክርና በኤዲቲንግ ሥራ ድጋፍ ያደረገልኝ ወዳጄ
ክቡር አቶ ኪዳኔ አለማየሁ ያላቋረጠ ድጋፍ የሰጡኝ አቶ
ይልማ ዘርይሁን፤ አቶ በትሩ ንብረእግዚአብሔር፤ አቶ
ተፈራወርቅ አሰፋ፤ አቶ ፍቅረማርያም ደረሰ በተጨማሪም
በዳላስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ሬዲዮ የታሪክ ክፍለ ጊዜ
ከ15 ዓመት በላይ የተባበሩኝን አቶ ዘውገ ቃኘው፤ አቶ
ሰጦታው በላይ አቶ ግርማ ንጉሤና የዳላስ
ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ሁሉ ከልብ አመሰናለሁ።

ይርጋዓለም ጎበዜ
የአዘጋጇ መብት በሕግ የተጠበቀ ነው

ስልክ ቁ. 214 293 2547
ኢ፣ሜል .....ansye214@a0l.com



ሀ -አዘጋጁ ከዚህ በፊት ለሕዝብ ያቀረባቸው1/.የአድዋ ድል የእቴጌ ጣይቱና የኢትዮጵያውያን የጀግንነት ታሪክ 2/. የዜግነት መጽሄቶች 3/.ይህ ይድረስ ለኢትዮጵያውያን የግጥሞች መድበል 4/. ስደተኛው ልዑል ቴያትር 5/. የትውልድ አደራ ቴያትር 6/. የታሪክ አደራ ቴአትር 7/. በዳላስ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ራዲዮ ኢትዮጵያ ታሪክ ፕሮግራም።

ለ -በጉዞ ላይ ያሉ መጽሐፎች 1/.የኢትዮጵያ ታሪካዊ ታሪኮች 2/.ልዩ ልዩ ገጠመኞቼ 3/. የታሪክ አደራና የትውልድ አደራ ቴትር፤ 4/.የጉራጌ ሕዝብ ማንነት።



አዘጋጅ ይርጋዓለም ጎበዜ

ዋጋው $15-